# ሀ/ ሀገር ገዳይ የሆኑ ድርጅቶችን ገድለን መሞት የማይገባትን እናት ሀገር ማዳን አለብን!!

ኃይሌ መለሰ (ብ/ጄኔራል)

የእናት ሀገርህ አንድነት ተናግቶና የአንተም ማኅበራዊ ደህንነት ታውኮ 15 ዓመት ሙሉ ስትታመስ የኖርከው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

ከሁሉም በፊት የሰው ዘር ዳኛ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር የእስካሁኑን እንባህን እንደ ራሄል እንባ አሳዝኖት እንዲያዝንልህ፣ የጀግኖች ልጆችህንም መስዋዕትነት እንደአብርሃም መስዋዕት ወዶና ፈቅዶ እንዲቀበልህ፣ ጠላቶችህን ግን የአንተን ጀግኖች እየቀጠፉና አንተን ሰላም አሳጥተው እያዋከቡ በሁለመናህ አዳክመው ጥለው አደላድለው ለመቅበር በሳሉልህ ባለብዙ ጥርስ የችግር ሰይፍ ላይ ጥሎ እንዲበቀልልህ የአለኝን ጽኑዕ ዕምነት ከፍተኛ ቁጭትና መሪር ሐዘን በተቀላቀለበት ስሜት ልገልጽልህ እወዳለሁ::

በአሁኑ ወቅት የትኛዎቹ ናቸው የባህሪ ልጆችህና ጽኑዕ ወዳጆች? ብለህ ለመጠየቅና በእርግጠኝነት ለይተህ ለማወቅ በሚያስጨንቅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የወላድ መካንና አጋር የሌለኝ ብቸኛ ተቸጋሪ ነኝ እንዴ? ብለህ ራስህን እንድትጠይቅና እንደ ዲዮጋን በእዉነት ሰው የሆኑ ሰዎችን በመብራት እንድትፈልግ በሚያስገድድ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ እንዳለህ ጠንቅቄ አውቃለሁ:: ይሁን እንጅ ጠላቶቻችን እንድትሆንላቸው የሚፈልጉትን ሳትሆንላቸውና እንድታደርግላቸው የሚገፋፉህን ሳታደርግላቸው ከመቅረትህ ጽናት ጋር ለብሔራዊ አንድነትህና ለጋራ ህልውናህ በአንድነት ቁመህ በማካሄድ ላይ ያለኸውን ተጋድሎ ከወደፊቱ በድል አድራጊነት የመውጣትህ ብሩህ ተስፋ ጋር እያገናኘሁ በአብሰለሰልኩ ቁጥር እፅናናለሁ::

ለአንተ ሁለንተናዊ ነፃነት ወሳኙ አንተ ብቻ በመሆንህ ሕዝባዊ ግዴታህን በተቀናጀ ሕዝባዊ ትግል እንድትወጣ የተማጽኖ ጥሪ ያቀረብኩበት የዚህ ጽሑፍ አርእስት <u>«አገር ገዳይ ድርጅቶችን ገድለን መሞት የማይገባትን እናት አገር ማዳን አለብን»</u> የሚል ግንባር ቀደም ጥሪ የያዘ ነው:: የተቀናጀ የሕዝባዊ ትግል ጥሪ እያቀረብኩ ድርጅቶችን መግደል አለብን ማለት እርስ በእርሱ የሚቃረን ሊመስል ይችላል:: አባባሉ ግን እንደ አንባቢው አመለካከት ካልተተረጎመ በስተቀር የሚቃረን ቀርቶ የሚያሻማ ትርጉም እንኳ የለውም:: አሥመሬበት የምገልፀው መለዕክት ሲገድሏት የኖሩትን ድርጅቶች ገድለን ሊያድኗት ቆርጠው የተሰለፉትን ድርጅቶች አጠናክረን በመቀጠል አደጋ ላይ ያለቸውን እናት አገራችን ማዳን አለብን የሚል ግልጽ ጥሪ ነው::

በአጭሩ አመላክቸ የማልፈው ጠቋሚ ነጥብ ቢኖር ግን አንድ በሺተኛ ሰው የችግሩ መነሻ መሠረታዊ ምክንያት ሳይታወቅለትና ለበሺታው ፍቱን መድሃኒት ሳይገኝለት ከበሺታው እንደማይድን ሁሉ የአገራችንም ችግር መታየት ያለበት ከዚህ አንጻር ነው:: ስለዚህ በመካከላችን ጤናማ ሕይዎት እንዲፈጠር፣ ጤናማ አስተሳሰብ እንዲሰፍንና በጤና ሠርቶ መኖር እንዲቻል ከተፈለገ ትውልድ በካይ የሆኑትን የዘመኑን በሺታች ጤና ካሳጡት ጤናማው ሕዝብ ማግለል የግድ ነው::

እንደሚታወቀው የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ከከፋፍለን እናዳክምህ እስከጨርሰን እናጥፋህ ባይ ባለብዙ የማጠፋፊያ ቋንቋ ተናጋሪዎች የክህደት ዓላማ አራማጆች የሰፋና የተወሳሰበ ነው:: የእነሱ ተከታይ ሆኖ ለድርጅታቸው እንዲሰግድላቸው እየገፋፉ ግራ የሚያጋቡት ጣዖት አምልኪዎችም የዘመቻው አካል፣ አባልና አጠናካሪ ኃይሎች ናቸው:: ይሁን እንጅ ሕዝቡ በሕዝብ ተተኪነቱና በሕዝብ ተኪነቱ ተፈጥሯዊ ግዴታ ለዘመናት ተሣሥሮ የኖረባትን ባለብዙ ድር ህብረ ቀለማት የአንድነት ማተብ አጥብቆ በማሠር የእናት አገሩ የማይናወጥ ጽኑዕ መሠረት ሆኖ የመጠበቅ ሐላፊነት ያለበት ባለሀብት መሆኑን እነዚህን ሁሉ አሳጥተን እናደህይህና ፍፁም አባብደን እናቆራርጥህ ብለው በዘመቱበት የአገር ጥፋትና የሕዝብ እልቂት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ተጠቃሚዎች ተጎትቶ የሚወድቅም ሆነ ተማርኮ እጅ የሚሰጥ አለመሆኑን ባለፉት አስተዛዛቢ ዎቅቶች የጋረጡበትን ችግሮች ሁሉ ተቋቁሞ በማለፍ አርቆ የማሰብ ታላቅነቱን አረጋግጠዋል ብየ አምናለሁ።

እንዲህም ሲባል ችግር ፍፁም አልነበረም፣ ወደፊትም አይኖርም ብሎ ለመደምደም አይደለም። በግድ ተጣሉ ብቻም ሳይሆን ተዳሙና ተገዳደሉ ተብሎ በታወጀው ይፋ አዋጅ ግፊት የተፈፀመው አፈራራጅ ድርጊት የቀደም ተከተል ጉዳይ ካላጠያየቀ በስተቀር ማን ብቸኛ ተጎጅና ተጠቂ፣ ማን ደግሞ ብቸኛ ተጠቃሚና አጥቂ እንደሆነ ሰጥቶ ያለፈው ትምህርት መቸውንም ቢሆን መዘንጋት እንደሌለበት አጠንክሬ ለማሳሰብ ነው።

ለጊዜው ጊዜው ሆኖናል ብለው በሌሎች መጎዳት እየተደሰቱ እራሳቸውን የሚያታልሉ ጊዜያዊ ተደሳቾች ካሉም የችግሩ ቀለበት ዙር ሠርቶ እስከሚገጥምና ፍርድ የሚሰጥበት የግፍ ደም ሞልቶ እስከሚፈስ እንጅ ሌሎችን በችግር ሲያል ውስጥ አጉረው እያቃጠሉ እነሩሱ ብቻ የሚኖሩባት *የመንደር ገነት* ፈጥረው ለመኖር የሚችሉበት መንፈሳዊ ብቃት ያላቸው አይመስለኝም። አለን ካሉም የሳጥናኤል ዓይነት ሙከራ ሊሆን ስለሚችል ወደመቀመቅ የሚያወርድ ፈተና እንጅ በከንቱ ለሚቃዡለት ገነት የሚያበቃቸው በጎ ሥራ እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ።

በመሠረቱ ይህች ዓለም በራሷ ምህዋር እየዞረች የዞረችባቸውን ናላ አዙራ ጥላ አዲስ በመተካት የማያቋርጥ ዙረቷን የምትቀጥል በመሆኗ ቋሚ ጠላትም ሆነ ዘላቂ ወዳጅ ያላት አይመስለኝም። ሌላው ቢቀር መቸና እንዴት አዙራ እንደምትጥላቸው ተፈጥሯዊ ሚስጥሯን በእርግጠኝነት የሚያውቅ ስለሌለ ዓለምን ጨብጠናል ይሉ የነበሩት ዓለማውያን ሁሉ ወድቀው መንኮታኮታቸውን ያወቀት ቁስሉ እየወጋ ማሰቃያቱን ሲቀጥልና ውርደቱ ተጭኖ ይዞ አላፈናፍናቸው ሲል ነው። የሰው ልጅ ግን እኖር ባይ ተስፈኝነቱና አልበቃኝም ባይ ራስ ወዳድነቱ ስለሚገዛው ካለፈው ተምሮ በእርሱ ላይ እንዳይደገም ለማድረግ ያለው ዝግጁነት አናሳ ነው። አንዳንዶቹማ ከነጭራሹም አልሠራላቸውም። ከዚህ ይልቅ ዞሮባቸው እስከሚወድቁ ድረስ መንገታገቱን ስለሚመርጡ ቀደም ሲል ሰው መስለው ከሰዎች ጋር የኖሩበትን ቅርፀ - ሰውነት ይተውና የቆሰለ አውሬ ሆነው ሁሉንም ነክሰን እናቁስለውና ገለን እንጨርሰው ወደሚለው አይቀሬ የጣዕር መንፈራገጥ ይለወጣሉ። ይህም ማለት የግብዓተ መሬታቸውን መቃረብ አመልካች ሀቅ እንጅ ተጠናክሮ የመቀጠላቸው ምልክት አይደለም። ስለዚህ ምንም ይሁን ማን ከዚህ የቅራኔ ሕግና የታሪክ ሂደት ውጭ መሆን ስለማይቻል የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን የሹም ሽር ሂደት ሕግ ተጠቅሞ ትግሉን አጠናክሮ በመቀጠል ድሉን ማቃረብ እንጅ አዲስ ነገር አድርጎ ማየት የለበትም።

የመልዕክቴም ዓላማ እነዚህን ሁሉ በማዘከር ወደፊት ለምታካሂደው ወሳኝ ትግል ወዳጅና ጠላቶችህን በሚመሳሰሉበት የቆዳ ቀለማቸውና በሚያስመስሉበት የቋንቋ ብዛታቸው ሳይሆን ተሰላልፎ በሚያሰያይፍ የክህደት ዓላማቸውና እኩይ ድርጊታቸው ላይ ተመሥርቶ ለመፋለም የሚረዳህ በብዙ ችግር የተፈተነ ልምዴን ለማካፈል ነው።

በጽሑፌ ስለጠንካራ ልጆችህና ጠንካራ ጎናችን ብዙም አላተኩርኩም። ምክንያቱም አጠያያቂ የሆነው ደካማ ጎናችንና ዝንጉርጉር የመጠፋፊያ ግብራችን በመሆኑ ነው። ስለጥንካሪያችንማ እኔ ባልገልፀውም ራሱ የትግሉ ውጤት ቆሞ የሚነበብና ቃል አውጥቶ የሚናገር ከመሆኑም አልፎ በታሪክና በትውልድ ሲዘከር የሚኖር የክብር ሥራ ክንውን መሆኑን ስለማውቅ ነው።

ስለዚህ በአብዛኛው የማተኩረው በወቅቱ ሁኔታ ላይ ተመሥርቼ ከትናንት እስከዛሬ የቀጠሉትን ተዛማጅ ችግሮች ጭምር የሚዳስስ ይሆናል። ምክንያቱም አንድ ዓይነት የሆነውን አገርን ተረባርቦ የማፍረስና ትውልድን ደም አፋስሶ በጠላትነት የሚያሰላልፍ ዘመቻ ለየራሳቸው በሚስማማ አባባል ከመገለፃቸው በስተቀር



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ቀደምቶቹን እነመለስ ዜናዊዎች ከዛሬዎቹ ልምድ ወራሾች ለይቶ ለማየት ስለማይቻል ነው::

በዚህም ምክንያት ጽሑፌ ሁሉንም የሚነካካ ነው:: ሁሉንም የሚነካካ ነው ስል ግን ግብራቸው የሚያስነካቸውን እንደባህሪያቸው እየለየ የሚያመለክት መሆኑን ለማመልከት ነው:: ይህን ሳደርግ አትንኩን ባይ የዕድሜልክ በሽተኞችን ቀድሞ ስለሚነካቸው እንደልማዳቸው አውካክተው እንደሚነሱብኝና የትናንቱን የነገር ጦርነት እንደሚከፍቱብኝ ካለፈው ድርጊታቸው በቂ ልምድ ያገኘሁ ስለሆነ አዲስ ነገር አይሆንብኝም::

ተፈጥሯዊ ባህሪያቸውና ጣዖታዊ አምልኮታቸው ስለማይፈቅድላቸው ነው እንጅ መልዕክቴን በቅን ኅሊና ለማየት ከቻሉ ግን ጠላታቸው የራሳቸው በሀገርና በወገን ላይ ሲፈጽሙት የኖሩት ኢትዮጵያዊ ዕምነት የጎደለው ክህደትና ሰብአዊነት የሌለው ድርጊት እንጅ ወንጀሉ ሲፈጸም ቁሜ ያየሁትና በእኩይ ድርጊታቸው ያረጋገጥኩት የህግ ምሥክር ልሆን አይገባም:: መጠያየቅ ያለብን መደረግ የማይገባው ድርጊት ተፈፅሟል? ወይስ አልተፈፀመም? የሚለው ነው:: አንድም አልተፈፀመም፣ አለበለዚያም ቢፈፀምም እኛ በወንጀሉ የለንበትም የሚሉ ካሉም መድረክ ይዘጋጅልኝና ንጹህ ነኝ ያለ የመጀመሪያውን ድንጋይ ያሳርፍብኝ:: የቃኤሎችን ድንጋይ ግን አልቀበልም:: ምክንያቱም እነርሱ ያለምክንያት ሰዎችን ሲገድሉና ሲያስገድሉ የኖሩ ቀታዮች ናቸውና::

በግልፅ እንደሚታወቀው የሀገራችን ችግሮች እየበዙና እየተወሳሰቡ መጥተው ከዚህ በእጅጉ ከሚያሳስብ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ካደረጓቸው ግንባር ቀደም ችግሮች አንዱ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነት የሚሰማቸው ወገኖች የሚጀምሯቸውን ሕዝብ - ጠቀም ሥራዎች በኢትዮጵያዊነት ስም የሚነግዱ ወገን መሰል ጠላቶች ተረባርበው እየዘመቱ በማፍረስ ሕዝባዊ ትግሉ ተጠናክሮ እንዳይቀጥልና የተሸለ አማራጭ እንዳይኖረው በማድረግ ነው:: እንዲህ ያለው የለየለት የጠላትነት ዘመቻ ደጋግሞ የተከሰተና በአሁኑም ወሳኝ የትንቅንቅ ወቅት በትናንቶቹ ልማደኞች ልምድ የተደገፈ ተመሳሳይ ክህደት በሌላ አሳሳች ቅርፅና ቀለሙ መቀጠሉ በገሃድ እየታየ ስለሆነ ይህስ አልተደረገም የሚል ክርክር የሚያስነሳ አይመስለኝም:: በእኔ ላይ የደረሰውን በዋቢነት ብጠቅስ የአድራጊዎቹ የጠላትነት ድርጊት ተጨባጭ ማረጋገጫ ከመሆኑ በተጨማሪ ወደፊት ለሚካሄደው ትግልም የቅድመ ማስጠንቀቂያ ትምህርት ይሰጣል ብየ ስላመንኩበት በአጭሩ ጠቅሸዋለሁ::

በውል ይተወቃል ብየ እንደምገምተው በዘመናት ጠላትነታቸው ወደታወቁት የሱዳኖች አገር ይሁንብኝ ብየ ቆርጬ እንድሄድ የተገደድኩት በዙሪያ - ገባችን ታጥረን የተያዝን በመሆናችን መፈናፈኛ መንገድ ከማጣቴ በተጨማሪ በወቅቱ በሁለቱ የቃል ኪዳን ወዳጆችን የስትራቴጂካዊ ግብ አጋሮች በሆኑት የሱዳን መንግሥትና የትግራይ ወያኔዎች መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ጊዜያዊ ቅራኔ በመጠቀም ወደነበርኩበት የትግል ግንባር ፈጥኘ ለመመለስ የሚያስችለኝን እቅድ አልሜ ነበር:: የመልክአ - ምድራዊ አቀማመጡ ማራኪነትና የሕዝቡም የኅብረት ግንባር ጥያቄ ግፊት በአሰብኩት እንድገፋበት እንጅ ሌላ አማራጭ እንዳማትርና ስጋቴ አይሎ ወደ ኋላ እንድል በአማራጭነት ያቀረቡልኝ አልነበረም::

ስለሆነም ከዚህ እናት አገርን ለማዳን ከታለመ ራዕይ ውጭ አንድም የተናገሩትን ያህል ሆነውና በተናገሩበት ቦታ ቆመው መገኘት ከማይሆንላቸው በእውነትም ሱዳኖች ከሆኑት ሱዳኖች ጋር የዘለቄታ ፍቅር ይመሠረታል የሚል ዕምነት ኖሮኝ አለነበረም:: አሊያም አንጋፋ ነን ባይ የባዶ ስም ቱጃሮች በባዶው እየጮሁ ሲያደርጉ እንደኖሩት የደመኛ ጠላቶቻችን አገር እንደእነርሱ አደላድሎ የሚያኖር ምቾት ሰጥቶኝ ጣምራ ንግድ እያካሄድኩ ለመክበርና ፉል እየበላሁ እንደእነርሱ እስከምነፈልል ድረስ ለመኖር አስቤ አልነበረም::

በየሄድኩበት ፈተናውን የማያሳጣኝ አምላክ የተመሰገነ ይሁንና እንደሄድኩ ያቀድኩትን ፈጥኘ እንዳደርግ እድሉንም አልነፈገኝም:: በእርግጥም እናት አገር



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ኢትዮጵያን ወደ ጥንታዊ ታሪኳ፣ ስምና ክብረ - ወሰኗ የመመለስ ብቸኛ ዓላማ ያለው ሕዝባዊ የኅብረት ግንባር ከሌሎች የዓላማው ደጋፊ ኃይሎች ጋር መመሥረት የሚያስችሉ ቅድመ - ሁኔታዎችን አመቻችተን በየፈርጁ መካሄድ የሚገባው ሁለንተናዊ ትግል ቀጥሎ ነበር:: በአጭሩ እኔም ብቻ ሳልሆን ታሪክና ትውልድ ሲናገሩለት የሚኖር ክቡር ሥራ ተጀምሮ እንደነበር በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ::

ባለመታደል ግን «ለመልካም ሥራ ያልታደለ አዕምሮ ለማጥፋት የፈጠነ ነው» እንደሚባለው የእኔ የአጭር ጊዜ ጥረትና የኅብረት ግንባሩ አበራታች መልካም ጅምሮች ለረጅም ዓመታት በባዷቸው ሲኮፈሱ የኖሩትን ባዶዎችና የቃላት ጦርነት አዋጊዎች ሁሉ አጋልጦ እርቃናቸውን ስላስቀራቸው ከግብር አጋሮቻቸው ማለትም ከሌላዎቹ እነመለስ ዜናዊዎች ጋር በርቸት ተጠራርተው በእኔም ሆነ በኅብረት ግንባሩ ላይ ባካሄዱት የተቀነባበረ ዘመቻ ሁለታችንም አደጋ ውስጥ እንድንወድቅና ጠላቶቻችንን ከፍተኛ ስጋት ላይ ጥለዋቸው የነበሩት እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ በለጋነታቸው እንዲቀጩ ለማድረግ አስችሏቸዋል:: በአጭሩ ግን ተማምለን እንክዳውና ተረባርበን እናጥፋው ብለው በዘመቱብኝ ወገን መሰል ጠላቶች የደረሰብኝን ባለብዙ መልክ ችግር ታሪክረና ትውልድ ሲፈራረድልኝ ይኑር ብየ ከማለፈው በስተቀር ለምሬቱም ሆነ ለዓይነቱና ብዛቱ መግለጫ የሚሆነኝ ተመጣጣኝ ቃላት አላገኝለትም::

እንደ እኔ ቅን ኅሊናና ራሴን ያለቆጠብኩበት ገደብ የለሽ ጥረት ኢትዮጵያውያንን በኢትዮጵያዊነታቸው ማመንና ለጋራ ኢትዮጵያዊነታችን ኅብረት ፈጥረን እንታገል ብሎ መማፀን መብትና ግዴታን አጣምሮ የያዘ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነትን የእንወጣ ጥሪ በመሆኑ አርቆ ሚያስብና ተገላምጦ የሚያይ ኅሊና ላለው ሰው በደስታ የሚቀበሉትና በጽናት ቆመው የሚዋደቁለት ክቡር ሥራ እንጅ ለማጥፋት የሚረባረቡበት ወንጀልና ወንጀለኛነት አልነበረም:: ይልቅየ ሲያፈራርድ የሚኖር ከባድ ወንጀል የሆነውና ወደፊትም የሚሆነው በኢትዮጵያዊነታቸው የታመኑት ኢትዮጵያውያን የታመኑበትን ኢትዮጵያዊነት ያህል መሆን ሲያቅታቸውና አለን ሲሉ የነበሩት ዕምነትና ቃል ሲርድባቸው የሥውር ክህደታቸው መሸፈኛና የሸውራራ አመለካከታቸው ማስተካከያ አድርገው የተጠቀሙበት በተገላቢጦሽ የሚነበብ ዘመቻቸው ነው:: የኅብረት ግንባሩ ሌላው ተፈታታኝ የችግር ገጽታ እነዚህን በመሰሉ የብዙ አገር መንግሥት አምላኪዎችና የባለብዙ ተለዋጭ አገር ጌቶች ጭምር የታጀበ በመሆኑ ነበር::

**የተወደድከው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!** ቀደም ብየ እንደገለጽኩት በዘመናት ጠላትነቱ የሚታወቀው የሱዳን መንግሥት እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነት የማሰማቸውና የወገን ፍቅር ማተብ ጨርሶ ያላተበላቸው ወገን መሰል ጠላቶች ያቀነባበሩትን ሤራ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ታሥሬ እንድሰቃይ ከማድረጋቸውም በላይ በቀላሉ ዋኝቸ ለመሻገርም ሆነ ተራምጀ ለመድረስ ወደማልችልበት የዓለም ዳርቻ ወደሆነች አገር ተወርውሬ እንድጣል በማድረጋቸው የፈጠረብኝ ችግር ካንተ ጋር የነበረኝን ቅርብ አካላዊ ግንኙነት ስላቋረጠው ተስፋ ሰጭ ጅምሬን ተመልሽ ለማጠናከርም ሆነ ግንኙነቴን ለመቀጠል የማያስችል ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርጎብኝ እንደቆየ ገባ ብለህ ተረድተህልኛል ብየ እገምታለሁ::

በአጠቃላይ ግን በእነዚህና በሌሎችም ተደጋጋፊ ችግሮች አስገዳጅነት ድምፄ ጠፍቶና ኮቴየ ርቆ እንዲቆይ አድርጎታል:: ይህን ስል የቆምኩለትን ሰፊ አድማስ ያለው ሕዝባዊ ዓላማና ጣምራ ግዴታየን በመዘንጋት ነገር ዓለሙን ሁሉ ትቼ ዝም ብየ ተቀምጨ አሳልፌዋለሁ ማለት አይደለም:: ቀንበሩ ጠቦኝና እንደ ጥላየ በየሄድኩበት የሚከተሉኝ ጥላ - ቢሶች ስለታጠርኩ እንጅ የተፈጥሮ ግዴታውን ለአፍታም እንኳን በማያሳግረው ኅሊናየ ግን አንተንና እናት አገሬን ከማብሰልሰል ያቋረጥኩበት ቀን ከቶም የለም:: ምክንያቱም ለእናት አገሬ ያለኝ ከፍተኛ ፍቅርና የችግሮች መፈራረቅ የማያላላው ፅኑዕ ማተብ በዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 137 ቁጥር:

«*5. ኢየሩሳሌም ሆይ! አንችን ብረሳሽ በገና ይምጫዎትበት ቀኝ እጄ ይክዳኝ፣*
*6. አንቺን ባላስታዉስሽና ታላቅ ደስታየ አድርጌ ባልቆጥርሽ የመዘመር ችሎታየ ይክዳኝ*» የሚለውን መቸውንም ሆነ የት የማይታጠፍ የእናት አገር ቃል - ኪዳን ዘዎትር እያዘከረ ሲያብሰለስል ሚኖር በመሆኑ ነው::



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እንዴት እንደምኖር ቀረብ ብለህ አይተህልኝ ቢሆን ኖሮ ከአንጀት እንደምታዝንልኝ እርግጠኛ ነኝ። የዘወትር ኑሮየ ሐዘንና የኅሊና ቁስል ያልተለየው ነው። የምተኛበት አልጋ በግፍ የተፈጁት ወገኖቸ አጽም የተከሰከሰበት መስሎ ስለሚታየኝ ጎኔን እየወጋ የሚያቆስለኝ እንጅ ተመችቶኝ የምተኛበት አይደለም። የምበላውና የምጠጣው ምግብም ቢሆን የእነርሱ ደምና ሥጋ አቅልሞ ያመረረው መስሎ ስለሚታየኝ እንደ እሬት እየጎመዘዘኝ ለመኖር ስል ከመብላት ባለፈ በሠራአካላቴ ገብቶ ምግብ የሚሰጠውን ጣዕምና እርካታ የሚሰጠኝ አልሆነም በየ ብናገር አጋንኘ አቅርቤው ይሁን? ብየ ራሴን አልጠራጠረውም።

በተፈጥሮየ ራሴን የማስቀደም ጉጉት የለብኝም። በአስተዳደጌም አይደገፍም። እንዲህ ያለው ግብዝነትም ሆነ ለሚያልፍ ችግር ተቸንፌ የማያልፍ ስምን የመሥበር ደካማነት ቢኖርብኝ ኖሮ መጀመሪያውኑ ቁስሌን ተሸክሜ ደሜን እያዘራሁ ሄጀ የችግሩ የሰደድ እሣት ከሚለበልበው ሕዝብ መካከል ተገኝቸ አብሬ ለመቸገር ባልተጋፈጥኩም ነበር። በብዙ አጋጣሚዎች እንደገለፅኩት በዚያን ትንቅንቅ ወቅት ፊትለፊት ገጥሜ እንድፋለም የተገደድኩት በግሌ የሕይዎት ከሣ ከማስከፈል የሚደርስ ቀረቶ ኅሊናየን የሚወቅስ ጠፋት እንደሌለብኝ ባውቅም በጋራ የደርግ አመራር አባልነቴ ግን ሀገሬንና ወገኔን በድያለሁ ብየ ስለማምን ሕይዎቴን ጭምር ካሣ በመክፈል ከታቀደባቸው የማጥፋት ዘመቻ ለማዳን በሚካሄደው ሕዝባዊ ትግል የድረሻየን ለመወጣት ስል ነው። ዛሬም ቢሆን በኑሮየ ተመችቶኝ ተደላድየ የተቀመጥኩ ሳልሆን በአንድ እግሬ ተንጠልጥየ ቆሜ መሹለኪያ ቀዳዳ የሚሆነኝን አጋጣሚ ለማግኘት በማፈላለግ ላይ ያለሁ ነኝ። ትናንት የምታውቃቸው የዓላማ ፅናት፣ የሞራል ጥንካሬና ብሩህ ተስፋ ዛሬም ከኔው ጋ አሉ። ከእኔ የሚያለፉት እኔ ሳለፍና በሥጋም ብቻ ሳይሆን በባህርይ ጭምር ለወለድኳቸው ልጆቼ ሲተላለፉ ነው።

በእርግጥ በዚህ መካከል ሌሎቹ አዘውትረው ሲያደርጉ እንደሚታየው በስም መኖራቸውን ብቻ ለማሳዎቅ ሲሉ ወረቀት እያዥጎረጎሩ መበተንና ቃላት እያሣረሩ መፎከር፣ አደንቋሪ ደወል እያቃጨሉ ያልተገኘ ለውጥና የተስፋ ምግብ እየመገቡ ሕዝብን ሲያታልሉና በስሙ ሲነግዱ የመኖር ዕመነቱም ሆነ ልምዱ ስለሌኝ አላደረግሁትም።

እንዲያውም ወገናቸውን የመንከስና የማራከስ ሱስ ያለበቸው ሰው መሰል ለማዳ አውሬዎች ኢትዮጵያን ለመሰለች ታሪካዊት አገር ቀርቶ የቤተሰቦቻቸውን ከብቶች እንኳ ከተሰማሩበት ስምር በወጉ ከትረው (ጠበቀው) ለማዋል የሚያስችል የሐላፊነት ብቃት የሌላቸው ተራ እረኞችና በፈታኝ ጎራ አሰልፎ የሚውል የሞራል ዳረጎት የሌላቸውን የመንደር አውደልዳይ ከርሣሞችን አብረው እያጫጫሁ እንዲያናክሳቸው ፍርፋሪ እየጣሉ አሰልጥነው ባዘመቱብኝ ቁጥር «ያዝ ቡቺ!» ብለው እነማን እንዳሠማሯቸው ጠንቅቄ ስለማውቅ ልማደኞቹ ነገር አዳኞች የሚጠብቁትን የነገር ገበያ አመቻችቼ ሲያተርፉ የኖሩበትን የነገር ንግድ ለማጧጧፍ የሚያስችላቸው ዕድል ላለመስጠት ስል ያለፍኩት የትዝብቴ አንዱ ፈርጅ አድርጌ ነው።

እኔ በእኔነቴ ግን አዘውትሬ በብርቱ የመጠነቀቀው በእምነቴ፣ በተናገርኩበት ቦታ በሚያቆመኝ ቃሌና እኔነቴን ስገልጽበት በኖርኩት ተግባራዊ ሥራየ መካከል ተጣጥሞ እየሄደ ዳር የሚዘልቅ እንጅ እርስ በእርሱ እየተጣረዘ ተፍረክርኮ ወድቆ የሁላችንም ምሥክርና እንደሥራችን ፈራጅ በሆነው ታሪክና ሕዝብ ዘንድ ሀፈረት ላይ የሚጥለኝ ድርጊት እንዳልፈጽም ነው። ተፈጥሯዊ ኅሊናየም ሆነ የሞራል ግዴታየ ከዚህ ውጭ እንዳደርግ አይፈቅዱልኝም።

ስለሆነም የህን ዕምነቴን ከተግባራዊ እንቅስቀሴ ጋር አዋህጀ ለመግለጽ የሚያስችሉኝ ሁኔታዎች እስከሚመቻቹልኝ ድረስ በትዕግሥት መጠበቅ የግድ ነበር። ዛሬም ቢሆን ችግሮቹ ሁሉ ተቃልለውልኝና የሤረኞቹ ሥራይ መቀመሚያ መርዝ ተነቅሎ ደርቋል የሚል ግምት ኖሮኝ ሳይሆን በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ለአለው ሕዝባዊ ትግል ሁኔታው የፈቀደልኝን አስተዋጽዖ ማድረግ ግዴታየ ስለሆነ ነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

## ለ/ የአሁኑን ትዉልድ በሚመለከት፣

***በአረመኔዎች እጅ ወድቀህ የምትሠቃየው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!*** ሁለተኛው የጽሑፌ አቢይ ርእስ ያሁኑን ትውልድ የሚመለከት ነው:: በአጭር አባባል እናት ሀገር ኢትዮጵያን ለማዳን ከሚስያስችል መሠራታዊ መፍተሄዎች አንዱ ከቀደምት አባቶቹ የተረከበውን ታሪካዊ አደራ ባለማክበሩና የተተኪነት ግዴታዉን ባለመወጣቱ ፈተና ውስጥ የወደቀው ይህ ትውልድ ራሱን ሊወቅስና ከድክመቱ መማር ሲችል ነው:: በእርግጥ ይህ አባባል ***«እንዲህ ያለው የህሊና ዝግጅትማ ካለ መጀመሪያውኑ ፈተናው መች ይመጣ ነበር»*** የሚል ጥያቄ ካላስከተለ በስተቀር ድክመቱ ግን ጭራሽ የለም የሚል ክርክር የሚያስነሳ አይመስለኝም::

ይህ ርዕስ ሰፊና ከበዙ ነገሮች ጋር የተያያዘ በመሆኑ የመስኩን ባለሙያዎች ምርምር እንደሚጠይቅ ይገባኛል:: እንደእኔ ግንዛቤ ግን ርዕሱን በአጭሩ ስተረጉመው የትዉልዱን የሁለት ጎን ደካማነትና የሁለት ጊዜ ተጎጅነት የሚያመለክት ይመስለኛል:: የመጀመሪያው አደራ - በልነቱንና የግዴታውን አለመወጣት የሚያመለክት ሲሆን ሌላዉ ለሚተካው ትውልድ የማያስብ ራስ ወዳድነቱንና የሚያወረሰው ጥሪት የሌለው ሁለንተናዊ ድህነቱን ነው:: በዚህ ላይ ተመሥርቼ በዝርዝር ለመግለጽ የምሞክረውም በመስኩ ሞያው አለኝ ብዬ ሳይሆን ሞያን ሳጠይቅ በገሃድ ስለሚታይ ሁለንተናዊ መናጋትና ቀለበት ሠርቶ እየዞረ አዙሮ ስለጣለን የትውልድ ዝቅጠት ነው:: ይሄ ደግሞ የማንም ኢትዮጵያዊ መብት ብቻም ሳይሆን ግዴታም ስለሆነ ባየኋቸው አስተዛዛቢ ድርጊቶች ላይ ተመሥርቼ ያለኝን አስተያዬት ብሰጥ ከድክመቱ መማር ለሚፈልግ ወገን ገንቢ እንጅ አፍራሽ አይመስለኝም::

በርዕሱ ወደሚካተቱት አቢይ ነጥቦች ከማምራቴ በፊት ትምህርትንና ትውልድን በሚመለከት ያለኝን አመለካከት በቅድማያ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ:: በመሠረቱ ለተማሩ ሰዎች ያለኝ አክብሮትና አድናቆት እጅግ ከፍተኛ ነው:: በመንግሥት ሥራ የአገልግሎት ዘመኔ የገበየሁት የሥራ ልምድም ከእነረሱ ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ያዳበርኩት ነው:: በአጠቃላይ ግን የተማሩ ሰዎች ቀጣይ ትውልድን በዕውቀት ፈጥረው የሚያሳድጉ መልካም ወላጆች ከመሆናቸውም በላይ ዓለም እየተለወጠች የመጣችውና ከዚህ የስልጣኔ ደረጃ ላይ የደረሰችዉ በእነረሱ ምርምርና ፈጠራ መሆኑን ስለማውቅ ነው:: የህን ስል ግን አንዳንድ ምርምርና ፈጠራቸው የፈጠረዉን ጎጅ ጎን አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሳላገናዝብ ቀርቼ አይደለም::

እኛ ግን በሁለቱም በኩል ቢሆን አልታደልንም:: ምክንያቱም ትምህርትን በጠቃሚ ጎኑ ለመጠቀም ቀርቶ ለመጉዳት እንኳ ጥበቡም ሆነ የመጠበቡ ብልሃት የለንም:: ቢኖረንም በወገን ላይ የሚውል እንጅ በወገን ላይ የሚውሉትን ለመከላከል አይደለም:: በእኛ አገር ተለፍቶ የሚሥራበት ለእኛ የማይሆን ዓይኑን ላፈር የሚባልለት ከስንኩል አስተሳሰብ የሚመነጭ ተራ ጥላቻና አገርንና ወገንን ለይቶ ማየት የማይችል እውር ጠላትነት ነው:: የሄ ደግሞ የተማሩ ሰዎች አድማስ ያለው አመለካከት ሳይሆን የማይሞች ማሃይማዊ አስተሳሰብና የጠባቦች ጎዶሎ ዕመነት ውጤት ነው::

ሁለተኛው ነጥብ እኔ ትውልድን የመስደብ፣ የተማሩ ሰዎችን የመንቀፍና የነፁሓንን ስም የማጉደፍ ዓላማም ሆነ ፍላጎት ፈፅሞ የለኝም:: ለእንዲህ ያለው እኩይ ድርጊት የተዘጋጀ ተፈጥሮም የለኝም:: እንዲያውም ይህን ለማድረግ ለተካኑና ሲገለገሉበት ለኖሩ ግብዞች አዝንላቸዋለሁ:: ምክንያቱም የንፁሓን መበከያ የሚሆን ጥላሸት እንጅ ማሳመሪያ የሚሆን መልካም ቀለም መለየት የሚችል ጤናማ ኅሊና ሳያድላቸው በመቅረቱ ነው:: በዚህ ምክንያት ዋነኛ አትኩሮቴ በኢትዮጵያዊነት ስም በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ሲካሄድ የኖረን ሲያፈራርድ የሚኖር ገሃድ ወንጀል መግለፅና ለቀጠለው ችግር መግቻ የሚሆን መፍትሄ መጠቆም ነው:: ይሄ ደግሞ በድርጊቱ ተጠያቂ የሆኑትን ብቻ የሚመለከት እንጅ ሞያንና ትውልድን የሚያጠቃልል አይደለም::



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በእኔ ዕምነት ይህ ትውልድ የታሪክ ዕዳ የማይከብደው፣ ኢትዮጵያዊ ሀላፊነት የማይሰማውና አብሮን እየኖረ አብረን እንድንኖር ላደረገን የወንድማማችነት ፍቅር በጎ አመለካከትና ተገቢ አክብሮት የሌለው ግለኛ ትውልድ ነው። ትውልድ ስል ግን በግልፅ አስምሬበት የምገልፀው የተወሰነ ዕውቀት በመገብየቱ ብቻ የሚመካውን፣ በፖለቲካው መድረክ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ወደሚፈልገው አቅጣጫ ለመጠምዘዝ ሲያጠማዝዝ የኖረውን በየደረጃው የስልጣን እርከኖች ተኮልኩሎ የሃላፊነትና የሞያ ግዴታውን በሚገባ ያልተወጣውን፣ በአጠቃላይም ለአገራቱም ሆነ ለሕዝቧ እኔ ብቻ አውቃለሁ እያለ አገር አጥፊና ትውልድ ገዳይ የሆነውን ወረቀት አምላኪ ትውልድ ማለቴ ነው። ከዚህ ባለፈ ወልዶ ማሳደጉና አስተምሮ ለየደረሱበት ደረጃ ማብቃቱ ጥፋት ሆኖበት ሊያጠፉት ሲጥሩ ለኖሩ ጠላቶቹ ተላልፎ ተሰጥቶ የሚሰቃየውን ውለታ መላሽ ያጣ ሕዝብ ማለቴ አይደለም።

ብትዝብት አምድ ስከታተላቸው ከነበሩት የአንድ ሰሞን ትኩስ የመወራከቢያ አጀንዳዎች አንዱን ለአብነት ያህል ብጠቅስ እስከአሁን ትውልድ ያልተካቸው ታላቁ ንጉሥ አፄ ቴዎድሮስ ከ150 ዓመት በፊት (በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ካለው የቅጥረኛ ባንዳነት ተልዕኮ ጋር በዓላማም ሆነ በአፈፃፀሙ ባይመሳሰልም) በአገሪቱ ላይ ተጋርጦባት የነበረውን ተመሳሳይ የብሔራዊ አንድነት ጥያቄ ችግሮች አስወግደው እስከአሁን ፀንታ ኖራ እንድንኖርባት ለማድረግ ያስቻሉን ምን ያህል ተቸግረው ቢቸገሩላት ነው? ብለው በመመርመርና መፍተሄውን በማፈላለግ ፋንታ የወቅቱ ቅድሚያ አጀንዳቸው አድረገው የዘመቱት የቴዎድሮስን የዘር ግንድ እንደመስቀል ደመራ ምሰሶ ወደሚፈልጉበት አካባቢ ለማዝመም ሲያካሂዱት የነበረው ግብግብ ነበር። ለነገሩ በቴዎድሮስ ስም የሚነግደው ሁሉ አንዱን ቴዎድሮስን፣ በቋራ ስም ሲነግዱ የኖሩት ሁሉ አንዱን ቋረኛውን መሆን ቢችሉ ኖሮ አንድ ለእናቱ ብቻውን ተፈጥሮ አንድ ብቻውን አንድ ያደረጋትን እናት አገር ብዙ ነን የሚሉ የባለ ብዙ ግብራም ወራሾች እንበታትናት ብለው ባልዘመቱባትም ነበር።

ይኸውና ትናንት የመጀመሪው የሰው ዘር መገኛ ሀገር ናት የተባለላት ታሪካዊት እናት አገር ዛሬ ግን የሰው ዘር መጠፋፊያና ማጥፊያ ብቸኛ ችግረኛ አገር እየሆነች ነው እንዲባልላት የተገደደችው ባለፉት ዓመታት በተካሄደው ዓላማና ውሉ ተለይቶ ባልታወቀ የዲቃ ዲቃ ጦርነትና በኢትዮጵያዊነት ስም ሲካሄድ በኖረው የፖለቲካ ንግድ ውድድር ድምር ውጤት መሆኑን የሚክዱ ቢኖሩ ለደረሰው ሁለንተናዊ መናጋትና የሕዝብ እልቂት ግንባር ቀደም ተጠያቂ መሆን ያለባቸው ወንጀለኞች ብቻ ናቸው።

ስለሆነም እነዚህን ሁሉ የተወሳሰቡ ችግሮች በውል ለመፍታትም ሆነ በእኛ ሁለንተናዊ ድክመት ተጠቃሚ የሆኑትን ጣምራ ጠላቶቻችንን በተባበረ ሕዝባዊ ክንድ መትተን ካለምነው ብሔራዊ ግባችን ላይ ለመድረስ የምንችለው :-

1. የምናካሂደው ትግል ዓላማና ትርጉሙ ጥርት ብሎ ሲታወቅ፣ ይህም ማለት እናት አገር ኢትዮጵያን የማዳን ሕዝባዊ ዓላማ ወይስ ድርጅታዊ ጣዖቶችን እንዳሻቸው እየሳሉ ሲያመልኩና ቁማር ሲጫዎቱ የመኖር ድብብቆሽ የሚለው ተሠምሮበት ሲለይ፣
2. ከደመኛ ጠላቶቻችን ጋር የድርጊት ግንባር ፈጥረው አብረው እየዘመቱ እናት አገራችን በሁሉም ጎኗ ተቀስፋ ተይዛ ኃይሏ እንዲደክምና ችግሩም ተውሰብስቦ ከዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ባለብዙ ፈርጅ አስተዋጽዖ ሲያደርጉ የኖሩትንና አሁንም ባማድረግ ላይ ያሉትን ወንጀለኛ ድርጅቶች ገድለን ችግሩን ፊትለፊት ተጋፈጠው በቁርጠኝነት በማዋደቅ ላይ የሚገኘ -ትን የሕዝብ ወገን የሆኑትን ድርጅቶች በማጠናከር መሞት የማይገባትን የብዙሓን እናት ሀገር ለማዳን ስንረባረብ፣
3. የተረከበውን ታሪካዊ አደራ ባለማስከበሩና የተተኪነት ግዴታውን ባለመወጣቱ ፈተና ውስጥ የወደቀው የአሁኑ ትውልድ ራሱን ሲፆቅስና ከድክመቱ መማር ሲችል፣
4. ሕዝብ ለአንድ አገር ሁሉም ነገር፣ ለሁሉም ነገር በሁሉም ነገር በመሆኑ ገደብ በሌለበት ሁለመናው የሚጠበቅበትን ባለብዙ ፈርጅ ሁለንተናዊ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ትግል አካሂዶ ለሁለመናው መብቃት ሲቻል ነው የሚል የእናት ሀገር እናድን ጠሪየን አምርሬ ለማሰማት ነው::

በእርግጥ የታሪክ አደራ በማይከብደው፣ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነት በማይሰማውና ለዘመናት አስተሣሥሮ ባኖረን አንድነትና ወንድማማችነት ላይ ዘምቶ ጥላቻና ጠላትነትን እያመረተ በመመገቡ ተብቶ የሰላምና የወንድማማችነት ፍቅርን ጣዕምና ትርጉም፣ የአንድነትን ኃይልና ክብር መለየት ባቃተው በዚህ ምስቅልቅሉ በወጣ ትውልድ ሕዝብ - ጠቀም የሆኑ ብሔራዊ ጉዳዮችን በተቀናጀ መልኩ ለመተግበር ሆነ የወል ጠቀሜታ ካለው ግብ ላይ ለመድረስ በእጅጉ እንደሚከብድ ደህና አድርጎ ይገባኛል::

ነገር ግን ዘላለማዊ ውርደት የወለደውን ባለብዙ ዕዳ አሳፋሪ ሞት አቅልሎ የተሸከመ ዕዳ አይከብድሽ ትውልድ ዘላለማዊ ነፃነትን ያህል ባለብዙ ዋጋ ክቡር ነገር አክብዶ ካየውና ጌታ መሆን ካስጠላው ምርጫው የእርሱ ነው ከማለት በስተቀር የሚሰማኝን መሪር ሐዘን መግለፅ የምችልበት ሌላ ቃል አላገኘሁትም:: ከዚህ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ውጭ ውጤትና ድል ያስገኛሉ ተብለው ተወጥነው የነበሩት ሁሉ ጊዜያዊ የራስ መሸጎገያ፣ የመዳኛ ጊዜን መግደያና የመልካም አጋጣሚዎች ማደናገሪያ ከመሆን እንዳላለፉ ካለፉት ዓመታት ተመክሮዎች አለመማር ማለት ሰው የሚያሰኝ ክቡር ሰውነትን ጥሎ ዕቃነትን መምረጥና የተገልጋዮቹ መገልገያ ዕቃ ሆኖ መኖር ማለት እንደሆነ ትርጉሙ የሚያሻማ አይመስለኝም:: ያውም የዕቃው ጌቶች ሲያደርጉ እንደሚታየው እንደፈለጉ ከተጠቀሙባቸው በኋላ «እነዚህ ጊዜው ስላለፈባቸው ይገለሉ» ብለው አንጋለው የሚጥሏቸውን፣ «እነዚህ ደግሞ ቀድመው የበሰሉ በመሆናቸው አንቀው የሚጥሉን እንጅ ጥመው የሚዋጡልን አይሆኑም» ብለው እየቀጠፉ የሚጥሏቸውን ሳይጨምር ማለት ነው:: ልብ ያለው እነዚህን ሁሉ አስቀድሞ ልብ ካላደረገ በስተቀር የሚያገኘው ትርፍ ቢኖር ከእንባም አልፎ ደም እያለቀሱና ጥርስን እያፋጩ የራስን አካል ሲነክሱ መኖር ብቻ እንደሚሆን በግብር ላይ ውሎ እየታየ ስለሆነ ሌላ ማረጋገጫ የሚያስፈልገው አይመስለኝም::

***መ/ ቅንጅት ማንም ለማጥፋት ስለዘመተበት የሚጠፋ ሳይሆን የሕዝብ አልፋ ወ ዖሜጋ ነው!!***

በመሠረቱ የቅንጅት ዓላማ ሕዝባዊ ዓላማ ነው:: ሕዝባዊ ዓላማ ደግሞ የሕዝብ ዕምነት፣ የሕዝብ ፍቅር፣ ፍላጎትና መብት ...ወዘተ የተዋሀዱበት የሕዝብ ሕይወት ማለት ነው:: ስለሆነም ቅንጅትን አጠፋለሁ ማለት ሕዝብን አጠፋለሁ ማለት ስለሆነ ሙከራው ቀርቶ መታሰቡ ራሱ በታሪክና በትውልድ ይቅር የማያባብል ከፍተኛ ወንጀል ነው:: ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የቅንጅት ዓላማ ሕዝባዊ ዓላማ በመሆኑ ይህን በግልፅ የተረዱና ለወገናቸው ብሩህ ራዕይ ያላቸው ኢትዮጵያውያን እንደሚደገፉት ሁሉ እኔም ሙሉ ድጋፍ አለኝ:: ይህን ስል ግን በድጋፍ ደረጃ እንጅ የቅንጅትም ሆነ ቅንጅት አዋህዶ አንድ ያደረጋቸው ድርጅቶች አባል አይደለሁም:: ቅንጅትን የምደገፈው ከላይ በጠቀስኩት ዓላማው ብቻ ሳይሆን ከሕዝብ መሃል ተወልዶ በሕዝብ ልብ የታቀፈ፣ በሕዝብ ተፈቅሮ በሕዝብ እንክብካቤ ያደገና ለቆመለት ሕዝብ ጥያቄ የተግባራዊ ምላሽ መሠረት የጣለ የሕዝብ አልፋና ኦሜጋ የሆነ ፓርቲ ነው የሚል ዕምነት ስላለኝ ነው:: እንዲህ ያለውን ሕዝብን በመውደዱና የሕዝብን ውሳኔ በማክበሩ በሕዝብ የተወደደና ለተጋረጡበት ችግሮች ቀድመው የተጋፈጡ ቆራጥ መሪዎች ያሉት የሀገርና የሕዝብ ነፃ አውጭ ፓርቲ ቀርቶ በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ የሚችሉትን ያህል ጥረት ለሚያደርጉት ሁሉ ከፍተኛ አክብሮትና ድጋፍ አለኝ:: በተቃራኒው ጎራ ተሰልፈው የጠላቶቻችንን የማፍረስ ዘመቻ ውጤታማነት በማጠናከር ላይ ባሉት የቅጥረኞች ተቀጣሪ ባንዳዎች ላይ ያለኝ ጥላቻ ደግሞ ከዚህ እጅግ የከረረ ነው:: ተጠልለው የተመረጡበትን ዓላማ፣ የመረጣቸውን ሕዝብና ያስመረጣቸውን ቅንጅት ክደው ወደ ጠላቶቻችን ጎራ የተቀላቀሉትን የለየላቸው ከሃዲዎች ቀርቶ ለአገሪቱ አንድነት መናጋት አስተዋፅዖ የምታደርግ ትንሽ የማደናቀፊያ ጠጠር የጣሉትንና የሕዝቡን ራዕይ የሚጋርድ ብናኝ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

አፈር የበተኑትን ሁሉ አምርሬ እጠላለሁ፣ አወግዛለሁም:: በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት ከመረጣቸው ሕዝብ ይሁንታ ውጭ ከጠላት ጋር ወግነው ተለጣፊ ቅንጅት በመፍጠር ቅንጅትን ለማፈረስና ቆራጦቹ የቅንጅት መሪዎች በወያኔው እሥር ቤት በስብሰው እንዲቀሩ ቀን ተሌት ደፋ ቀና የሚሉትን ማተበ - ቢሶች ከዚህ የክህደት ሥራቸው እንዲቆጠቡ አጥብቄ እያሳሰብኩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከእርሱ ይሁንታ ውጭ በስሙ ክህደት የሚፈፀምበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማተበቢስ ከሃዲዎች ሁሉ ትምህርት ሰጪ በሆነ መልኩ ተቃውሞውን ለከሃዲዎቹ እንዲያሳያቸው ጥሪየን አቀርባለሁ::

በንጉሡ የአስተዳደር ዘመን የሱማሊያ መንግሥት የኢትዮጵያን ድንበር ተጋፍቶ ጦርነት መክፈቱን የሰሙት የጎንደር አርበኞች እንዴት ተደፈርን ብለው በጣም በመቆጨት በሰልፍ ሆነው ከእንደራሴው ፊት ይቀርቡና አቅማቸውን ሳይሆን ያልደከመ ወኔና ሞራላቸውን ተማምነው እንዲያዘምቷቸው ይጠይቃሉ:: እንደራሴውም ባቀረቡላቸው «የምን ሲል ተሞክሮ» ጥያቄ በጣም ተደንቀው «እናንተ በጊዜያችሁ ግዳጃችሁን ተወጥታችኋል፣ አሁን ደግሞ ልጆች ስለተካችሁ የእነርሱ ድርሻ ነው:: ጦርነቱም ከሠራዊታችን አቅምና ችሎታ በላይ አይደለም::» ብለው በማነጋገር ላይ እንዳሉ አንደኛው አይበገሬ አርበኛ እልህ ተናንቋቸው ***«ገዳይ ሱማሌ! ገዳይ ሱማሌ! ...»*** እያሉ መፎከር ይጀምራሉ:: ጓደኞቻቸው አረጋግተው ይዘዋቸው ከወጡ በኋላ «ቀኛዝማች ዛሬ ከእርስዎ የማይጠበቅ ስህተት ተሳሳቱ፣ እርስዎ ወደ አድዋና ማይጭው ከጣሊያኖች ጋር እንጅ መቼ ወደ ሱማሌ ዘመቱና እንዲህ ብለው ይፎክራሉ?» ብለው ሲጠይቋችው አይበገሬው ቀኛዝማች ግን:- «***የተሳሳታችሁትስ እናንተ ናችሁ፣ ለእኔ አገሬን የወጋ ሁሉ ጣሊያን ነው::***» አሏቸው ይባላል::

እኔም እንደ እርሳቸው ኢትዮጵያን የወጋና የጎዳት ብቻም ሳይሆን ሊጎዳት ያሰበና በክፉ የሚያስባት ሁሉ ጠላቴ ነው:: የእኔም ብቻ ሳይሆን የእናት ሀገርና የሕዝቧም ጠላት ነው:: ሀገራችን አንድነቷ እየተናጋ ነው፣ ህዝቧም በአደባባይ እየተገደለ ነው ስንል ለእነዚህ ችግሮች መባባስና መጠናከር አስተዋጽዖ የሚያደርጉትን ችግሮች ሁሉ አጠቃልለን በማየት ይመስለኛል:: የወያኔ መሪዎች ከላይ ሆነው የሚያዙትን ከታች ያሉት ወታደሮችና ካድሬዎች ባይፈጽሙ ኖሮ ሕዝብ ሰላም አጥቶ ባልታወከና የሕዝብ ልጆች በየአደባባዩ ባልተገደሉም ነበር:: በሀገርና በሕዝብ ስም የሚነግዱ የፖለቲካ ደላላዎች ባይበረክቱ ኖሮ የሕዝቡ ጠንካራ ክንድ ባልዛለና ሲያካሂድ የኖረው ትግልም ፍጥኖ የማደግ ዕድሉ ተዳክሞ ባልቆየም ነበር::

ስለዚህ በእኔ ትርጉም መተኪያ በሌላት እናት ሀገርና የሰው ልጅ ሕይዎት ላይ ተጋግዘው የሚችሉትን ያህል የሚረባረቡ እስከሆኑ ድረስ ጠላት ያው ጠላት እንጅ ትንሽና ትልቅ ጠላት የሚባል ነገር የለም:: እንደሚታወቀው የቅንጅት ዕድሜ በወራት የሚቆጠር ቢሆንም ገና ከጅምሩ የተጋፈጣቸውን በርካታ ውስብስብ ችግሮች በበሰለ የአመራር ስልት እየተከላከለ ከሳይው ፈጣን ዕድገት በዙሪያው ካሰለፈው ኅብረ - ብሔር ሕዝባዊ ኃይልና ካስመዘገበው ታሪካዊ ድል አኳያ ሲገመገም ተአምር የሚባልለት የአጭር ጊዜ የፌትለፊት ተጋድሎ ውጤት ከመሆኑ በተጨማሪ ጡረታ የለሽ ዕድሜ ቆጣሪዎችንና ዕድገትና ውጤት የለሽ ድሃ ስመ - ድርጅቶችን ሁሉ እርቃናቸውን አስቀርቶ (ለነገሩ ዱሮም ቢሆን በምላስ ጮሌነት የተሸፈነ እርቃን እንጅ እርቃናቸውን የሚሸፍን የሥራ ልብስ ኖሯቸው አልነበረም::) ከፖለቲካው መድረክ ጨርሰው እንዲወገዱ በማድረግ ከሕዝብ በሕዝብ ለሕዝብ የተወለደ ብቸኛ የሕዝብ ፓርቲ መሆኑን በችግር ተፈትኖና በተግባር አረጋግጦ የወጣ ሆኗል የሚል አስተያየት ብሰጥ የአመራሩ አይበገሬነት፣ ጥንካሬና የሕዝቡ የተጋድሎ ውህድ ውጤት ያረጋገጠውን ገሃድ ዕውነታ መሠረት አድርጌ የተናገርኩት ስለሆነ በእንዲህ ያለው ያልጠበቁት ታሪካዊ ክንውን ተቀደምን የሚል ጥላቻ ካደረባቸው ወገን መሰል ጠላቶች በስተቀር አባባሌን በነቀፋ መልክ የሚያዩ የሕዝብ ወገኖች ይኖራሉ ብየ አልገምትም::

በመሠረቱ የቅንጅ አመራር አባላት የሕዝቡ ቁስል በብርቱ የሚያማቸው የሕዝብ ልጆች በመሆናቸው ችግሩን አብረው እየተጋሩ ያሳዩት አርአያነትና ያስገኙት ፈጣን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሁለንተናዊ ዕድገት የጠላቶቻችንን በአሸዋ ላይ የተገነባና በአየር ላይ የተንሳፈፈ የአንደፈርም ባይነት የትምክህት ሠፈር ባልጠበቁት ሁኔታ ከማናጋቱ ጋር ተዳምሮ ሲገመገም ነገር መፍተልና ሜራ ማሜርን እንደ ጠቃሚ የፖለቲካ ሥራ አድርገው ሲያወሩ በመኖርና የሕዝብን ችግር ለመቅረፍ አስተዋፅዖ ያላት ጥርኝ የምትሞላ ቁምነገር በመተግበር መካከል ሰፊ የዓላማም ሆነ የሥነ - ምግባር ልዩነት መኖሩን ግልፅ አድረጎ ያሳየና ጠቃሚ ትምህርት የሰጠ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ዓላማን ከተግባር ጋር የዋሀደ ፈጣን ለውጥ በአንድ በኩል ሁሉም እንደ ፈለገ ሲነግድበት ለኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለፈውን አዘክሮ ወደፊት እንዲጠነቀቅ ያስተማሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቁርጥ ቀን ልጆች መሆናቸውን ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ ቅንጅት ማለትምንና ማን እንደሆነ ወዳጆቻቸው ቀርቶ ጠላቶቻቸው እንኳ አምነው እንዲቀበሉየተገደዱበት ሀቅ ሆኗል፡፡ *«የሀገር ክህደት ወንጀል»* የተባለላቸውም በጠላቶቻቸው ከበባና ወከባ ላልተው ያልተንበረከኩ እናት ሀገር አድን የሆነ ብሔራዊ ዓላማቸውን ለድርድር ያላቀረቡና የቆሙለትን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ጠላቶቹ እንዲረግጡት ፈቃደኛ ሆነው ያላነጠፉ የእነዚያ የትናንቶቹ ሰው የሆኑ ሰዎች የባህሪ ልጆች የመሆናቸው ግልባጭ ነው፡፡

በእርግጥ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚነገረውና የሚደረገው ሁሉ በተገላቢጦሽ የሚነበብና በተቃራኒው የሚተረጎም ከሆነ አሥራ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ይህም በመሆኑ ይኸውና እናት ሀገር ኢትዮጵያን ከመሠረቷ አናግቶ ለማፈራረስና በታሪካዊ ጠላቶቿ ለዘመናት የተከማቸ በቀል መወጫ አድርጎ ግዳይ ለመጣል የዕቅዱ ግብ አድርጎ የተነሳው ከሀዲው መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ የቅንጅት አመራር አባሎችንና የብሔራዊ አንድነት ተጋዳይ አርበኞችን እያደኑ የገደሏቸው፣ ያሠሯቸውና በሀገር ክህደት ወንጀል የከሰሷቸው እንደሌሎቹ መሣሪያ አድርገው የማያገለግሉ ዕቃዎች፣ የማያፌዙባቸው በባደው ጯሂ አደንቋሪዎችና በቀላሉ የማይገፈትሯቸው ሕዝባዊ ኃይል የለሽ የወረቀት ሰዎች አልሆንላቸው ብለው አስጨንቀው ስለያዟቸው ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ዕውን ወንጃዮቹ አቻ የለሽ ወንጀለኞች ወንጀል አድርገው ያዩት እናት አገርን የማዳን ክቡር ነገርና ሕዝብን አስተባብሮ ያዘመተ ሰላማዊ ትግል የሚያስወነጅል ወንጀል ሆኖ አልነበረም፡፡

እንዲያውም የቅንጅትን አመራር አባላት ሳያስፀፅታቸው አይቀርም ብየ የምገምታቸው ተደጋጋፊ የሆኑ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች አሉኝ፡፡ የመጀመሪያው እንዲህ ያለውን ኅብረ - በሔር የሆነ ሕዝብ አስተባብረው ማዝመት የቻሉ አይበገሬ የአመራር ኃይሎች ዛሬ የጣሉትን ባለብዙ ፈርጅ ጠቀሜታ ያለው የዋነኛው ግብ መሸጋገሪያ መሠረት ከትናንት በፊት ጀምረውት ቢሆን ኖሮ ለኢትዮጵያ ችግር መኀለበትና የበለጠ መውሰብሰብ አስተዋጽዖ ሲያደርግ የኖረውን ጊዜ ከማሳጠሩ በተጨማሪ የተጣለው መሠረት በድል ተደምድሞ ለግብ የሚበቃበት ወቅት ይሆን ነበር የሚለውን መለስ ብለው ያዘክሩ እንደሆን ነው፡፡

በበለጠ ያስፀፅታቸዋል ብየ የምገምተው ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ዘምተው ታሪክ የማይፍቅላቸውና ትውልድ ይቅር የማይላቸው የክህደት ወንጀል ሲፈፅሙ የኖሩት የባለ ብዙ ጌታ ቅጥረኞች ሊያጠፏት አቅደው ከተነሱባት እናት ሀገርና አውካክተው ከዘመቱበት ሕዝብ ላይ የነጠቁትን የዓላማቸው ማስፈፀሚያ መሣሪያ (ሥልጣን) *«እስከአሁን ስንፈፅመው የኖርነው በክህደት የታጀበ ግፍና በደል ስለበቃን እንኩ ውሰዱ»* ብለው ይመልሳሉ ተብሎ መጀመሪያውኑ መታሰቡና የርክክቡ ሰላማዊ ትግል መጀመሩ ነው፡፡ የርክክቡ ሰላማዊ ትግል ስል ግን 15 ዓመት ሙሉ እንደፈለጉ ሲያብጠለጥሉት የኖሩት ደመኛ ጠላቶች ግፍ ሲፈጽሙበት የኖሩትን ሕዝብ ድምፅ አግኝተው በአቸናፊነት እንደማይወጡ አስቀድሞም ሳይቆጠር ተቆጥሮ ውጤቱ የታወቀ ስለነበር ይሳካል ተብሎ የተጀመረው ሰላማዊ ትገል በእርግጥ ይሳካልን? የሚል ጥያቄ ያጠላበት ስለነበር ነው፡፡

ይህን ስል ግን <u>*በተደራጀ*</u> ሕዝባዊ ኃይል የሚካሄድ ሰላማዊ ትግል ለውጤት አይበቃም በየ ለመደምደም አይደለም፡፡ ወደድል ምዕራፍ ሊያሸጋግር ለሚስያችል ውጤት እንደበቃም የራሱን የቅንጅትን አርአያነት ያለው ተጋድሎ በዋቢነት ጠቅሻለሁ፡፡ ነገር ግን ቀመሩ ተሟልቶ የሚሠራውና ትግሉ ሰምሮ ለዋነኛው ግብ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሚበቃው አንድም የታሪክን ፍርድ ከሚፈራ፣ ሕዝባዊ ወገናዊነት ካለውና ብሔራዊ ሀላፊነት ከሚሰማው፣ በአጠቃላይም አንድን አገር በመንግሥትነት ለመወከል የሚያስችል ሥነ - ባህርይና የሞራል ብቃትን ከሚያሟላ መንግሥት ጋር በስልጣን ትያቄ ብቻ ሰላማዊ ፍጥጫ ሲገጠም፣ አለበለዚያም ሕዝባዊ ትግሉ ራሱን መከላከል የሚችልበት ሁለንተናዊ የአደረጃጀት ባህርይ ሲኖረውና **«ከዚያም ቤት እሳት አለ»** ያሉትን የአባ ገብረሃናን ትምህርት ሰጭ አባባል ያዘከረ ሲሆን ነው የሚል አስተያየት አለኝ፣ አቋሜም ይኸው ነው::

ትናንት በልልነቱ ደህና ሆኖ የሚታወቀው መለስ ዜናዊ ዛሬ ግን ወደዓይኑ ጦር ቢወረወር እንኳ የማያረግብ ልበ ሙሉ ጀግና መስሎ የሚታየው የእሱ ተጥሯዊ ወኔ ፈቅዶለት ሳይሆን ልልነቱን የሸፈነለትና ማሣሪያ አድርጎ የሚገለገልበት መሣሪያ ስላለው መሆኑ ለአፍታ እንኳን መዘንጋት አልነበረበትም:: የጭካኔው ተፈጥሯዊ ሚስጥርም ይሄው ስለሆነ መፍትሄውም እሱን መላቀቅ እንጅ እሱን ከተፈጥሮ በሺታው ለማላቀቅ መሞከር አይደለም፣ ምክንያቱም አይቻልምና::

ይህ ሁሉ በገሃድ እየታወቀ የእኛ ችግርና ችግሩን እኛ ብቻ እንፈታለን ባዮች ሲፈትሉ የኖሩት ሁሉ ከሌሎች የተለየ በመሆኑ ሰላማዊ ትግሉም ከዚያ አንፃር ካልታየ በስተቀር የታጠቀ ጎሠኛ ሠራዊትና በሕዝብ ነፃነት ላይ የዘመተ ፋሺስታዊ መንግሥት ነጹሃንን በየአዳባባዩ በግፍ እየረፈረፈ ሲጥልና ጎዳናዎችን በደም ጎርፍ ሲያጥብ እንጅ የሕዝብ ቁስል አሞትና ብሶቱ ተስምቶት ስልጣኑን በሰላማዊ ትግል ሲለቅ የታየበት የታሪክ ክስተት ጨርሶ የለም:: ቅጥረኛ ባናዳዎችም ቀጥረው ካዘመቷቸው ጌቶቻቸው ከወረሱት ፋሺስታዊ ባህርይ ውጭ የትኛውን የመንግሥትነት መስፈርት ያሟላሉ ተብለው ግምትና ትርጉም እንደተሰጣቸው አልገባኝም:: ከብዙዎቹ አጠያያቂ ጥያቄዎች አንዳንዶቹን ለአብነት ያህል ብጠይቅ:-

1. የመጀመሪያው መሠረታዊ አጠያያቂ ጥያቄ ለመሆኑ የመንግሥትነት ሥነ - ባህርይ መስፈርቶችን የሚያሟሉና ታሪካዊት ኢትዮጵያን በመንግሥትነት ለመወከል የሚያስችል የሞራል ብቃት ቀርቶ ፍርፋሪ እንኳ አላቸው ወይ? የሚለው ነው:: አላቸው እንደማይባል በጣም እርግጠኛ ሆኝ፣ የላቸውም ከተባለ ደግሞ ታዲያ ከማን ጋር ነው ሰላማዊ ትግልና ድርድር ለማድረግ የተሞከረው የሚል ጥያቄ ማስከተሉ አይቀሬ ነበር:: ይኸውና አስከትሎም እየታየ ነው:: መልሱ ግን የጌቶቻቸውን ባህርይ ለማሟሸትና በሰላማዊ ትግል ስም ዙሪያውን በሚያደራው የዲፕሎማሲ አሽከላ ተጠልፎ በመውደቅ ለእናንተ ዴሞክራሲ የሚሠራው የቡችሎቹ ፋሺስቶች ባህርይ መጋረጃ ሆናችሁ እስካገለገላችሁ ጊዜ ድረስ ነው የሚል ሆኗል::

   እነሱ በእኛ ላይ ያላቸው አመለካከት አንድም ደህና ሆኖ ስላልገባን፣ አለበለዚያም እነርሱን ማምለክ ስለበለጠብን ካልሆነ በስተቀር የሰውን ልጅ ከዱር አራዊት ጋር እያጋጠሙ በስቃዩ ሲደሰቱ የነበሩ ሰዎች ተተኪ ልጆች የወቅቱን የሕዝብ (በተለይም የአፍሪካን) ችግር ቀላልና የአዲሱ ዘመን የዴሞክራሲ ዕድገት ውጤት አድርገው የሚያዩት እንጅ እንደችግር የሚቆጥሩት አይመስለኝም:: **«ዴሞክራሲ እኮ ቀስ በቀስ በመቁኑን እንጅ አንድ ጊዜ አይመጣም»** የሚሉንም ለዚህ ነው:: እነሱ ይህን የሚሉት ወደታች ጠልቀንና ወደላይ መጥቀን ዓለምን ጨብጠናታል ስለሚሉ ሌላው ስለዓለምም ሆነ ዓለማዊ ኑሮ የሚያይና የሚያልም አይመስላቸውም::

   በዚህም ምክንያት የእኛን ችግር የሚያዩት እንደጊዜ ማሳለፊያ መዝናኛ ቦታና እንደቁማር መጫዎቻ ካርታ ሊሆን ይችላል:: በዚህ ላይ ደግሞ የጠላትነት በቀሉም አለ:: አለያማ እኛም እንደእነርሱ ተደላድለን ቆመን ወደሩቅ አድማሳችን ማትኮር ከቻልን መጫዎቻዎች መሆናችን ይቀርና «እኛም አብረን እናጫውታችሁ» የሚል ጥያቄ ማቅረብ ስለምንችል ይህን ለማድረግ የምንችልበት ዕድልም ሆነ ፋታ አይሰጡንም:: ጠባብ መንደርተኞች እንዲፈጠሩና የመንደር ድርጅቶች እንዲፈለፈሉ በማድረግ እርስ በእርሳችን እየተናከስን ዘላለም ከስሰን እነርሱን ብቻ እያመለክን እንድንኖር



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሚያደርጉትም ለዚህ ነው:: ስለዚህ ማንም ተንከባክቦ ያሰደገውንና አሰልጥኖ ያሰማራውን ተናካሽ ውሻ ሜዳ ላይ ስለማይጥል ከእነርሱ የሚጠበቀው ተስፋ ዕውን መሆን ቀርቶ በተስፋነቱ እንኳ የሚያገለግል አልሆነም::

2. ወያኔዎች አቅደው የተነሱለትና አውካክተው የዘመቱለት ዓላማ ምንድነው? ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ሲሉ ባለፉት 15 ዓመታት ምን ሲያደርጉ ኖሩ? አሁንስ ምን በማድረግ ላይ ናቸው?
3. እነሱ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ለሚገለገሉበት ስልጣን የበቁት በትጠቅ ትግል ሆኖ ሳለ ተቃዋሚ ኃይሎች በብሔራዊ አንድነታቸውና በጋራ ህልውናቸው ላይ የሚካሄድባቸውን የጥፋት ዘመቻ ለመከላከል የሚያካሂዱትን የትጥቅ ትግል ለምን አምርረው ጠሉት? ሕዝቡንስ የክንድ መሣሪያ ቀርቶ መደገፊያ በትር እንኳ እንዳይኖረው በማድረግ በጀሌለነት ለመግዛት ለምን ፈለጉ?
4. ሰላማዊ ትግሉን ፈቅደናል ሲሉ የዕምነትም ሆነ የባህርይ ለውጥ አድርገው ነው? ወይስ ፋሺስታዊ ባህሪያቸውን የሚሸፍኑበት መሣሪያ አድርገው ለመገልገል?
5. ባለፉት ዓመታት ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ ጀምረው በነበሩት ድርጅቶችና አባሎች ላይ የተፈፀመው የለየለት የጠላትነት ድርጊት ለምን ተረሳ? ዛሬስ ያ እንዳይደገም የሚከላከል ምን አስተማማኝ ዋስትና ተገኘ? ሰላማዊ ትግሉ ባይሳካ ምን ሌላ አማራጭ የትግል ስልት አለ? ለዚህስ ምን ያህል ተዘጋጅተናል?
6. ሌሎችን ከሰላማዊ ትግል ውጪ ምን ሲል ተሞክሮ እያሉ ቀይደው ይዘው ራሳቸውን ግን «በጦርነት ተወልደን በጦርነት ያደግንና ጦርነትን መፍጠር የምንችል ነን» ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ለመሆኑ የጦርነት ፈጣሪ ሰላም ፈላጊ ሊሆን ይችላልን? ይችላል ከተባለም እንዴት ብሎ?
7. በመሠረቱ ወያኔዎች በስልጣን ላይ መቆየትን አጥብቀው የሚፈልጉበት እስትራቴጂካዊ ዓላማ ለማን ምን እስከሚያሟሉላትና እስከሚሟላላት ድረስ መሆኑ ግልፅ ነው:: ስልጣን ልቀቁ ሲባሉ ግን ለዕቅዳቸው ማሚያ የሚሆን ምን አማራጭ ቀረበላቸው? ወይስ «እንደጎደለባቸው» ይቅር ተብለው? ይህ ከሆነ ደግሞ ሰላም በኢትዮጵያ ቀርቶ በዓለም ላይ እንኳ ቢጠፋ እኛንም ጭምር የዞን ይጠፋ ይሆን ብለው የሚያስቡ አይመስለኝም::

በአጠቃላይ ግን ለእነዚህ ከችግሩ ጋር ለተቆራኙ መሠረታዊ ጥያቄዎች ትክክለኛ ትርጉምና ሁነኛ መልስ የሌለው ትግል ለግብ ይበቃል በየ አላምንም:: ይህን ስል ከእኔ በበለጠ ነገሮችን በጥልቀት መርምረው የሚያውቁት የቅንጅት አመራር አባሎች እነዚህንም ሆነ ሌሎችን ተዛማጅ ጥያቄዎች እያነሱ መፍትሄ ይሆናሉ ያሏቸውን መልሶች አስቀምጠውላቸው ሊሆን ስለሚችል የመገምገሙን ሃላፊነት የምተወው ለእነርሱው ነው::

ወያኔዎች የገጠመኞች መደጋገፍ የፈጠረላቸውን አጋጣሚዎች በመጠቀም ያገኙትን ሁሉ የልዩ ሰውነታቸው ውጤት አድርገው ራሳቸውን ቢያታልሉም ቅሉ ሥጋ ለባሲነታቸው የባህርይ አውሬነታቸውን ሊሸፍኑላቸው እንዳልቻለ ሁሉ ራሳቸውን የሚያታልሉበት ልዩ ሰውነትም ከማይቀርላቸው ዘላለማዊ ውርደትና የእርኩስ ሞት ከመሞት የሚያመልጡበት አንዳችም መንገድ የለም:: ይሄም ሆኖ ጥረታቸው እየገደልን እንገዛለን፣ እያጠፋን እንኖራለን ሳይሆን ከጠፋን አይቀር አጥፊተን እንጠፋለን ብለው የተነሱ መሆናቸው ነው::

ክህደት ያወረው ዕምነታቸው ማድረግ የሚገባቸውን ለይተው እንዳያውቁ ስላደረጋቸው ይጠቅመናል ብለው ያለአማራጭ የሚጠቀሙበት ስልት ዛሬ ማድረግ የምንችለውን አድርገን የትናንት ታሪክና የነገ ትውልድ የፈለጉትን የፍረዱብን ብለው እንዲመኩ ያደረጋቸው የዲያብሎስ ተከታዮች በመሆናቸው ይመስለኛል:: ይህ ባይሆንማ ኖሮ በሰፊው የሚያስቡ ታላቅ ሰዎች የመሩት ለሁሉም የሚበጅ ታሪካዊ ክንውን ሊባልለት የሚገባውን የሕዝብ ሰላማዊ ትግል ወንጀል፣ ከቡር ሰዎች የሚያሰኝ ዘላለማዊ ክብር ሊላበሱ የሚገባቸውን ከቡር ሰዎች ደግሞ ወንጀለኞች አድርገው ሊያዩአቸው ባልተገባቸውም ነበር::



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

አለበለዚያማ የሀገር ክህደት የከሃዲዎች ዕምነትና ባህርይ ስለሆነ በወዳጅነት የሚያስተቃቅፍ እንጅ በጠላትነት የሚያሰላልፍ ሊሆን ስለማይችል የከሃዲዎች መሪና አደራጅ ለሆነው መለስ ዜናዊና አጃቢዎች ታላቅ የምሥራችና ብዙ ትርፍ ያለው የፖለቲካ ሲሳይ በመሆኑ የሚጠብቃቸው ሹመትና ሜዳሊያ እንጅ እሥር ባልሆነ ነበር።

እንደሚታወቀው በድርጅቶች ቁጥር ብዛት ክብሮ የነበረው ኅብረት ተመሠረተ ተብሎ በሚናፈስበት አፍላ ወቅት ጋዜጠኞች መለስ ዜናዊይን ጠይቀውት ነበር። የሰጠው መልስ «... የትጥቅ ትግል የማያዋጣ ነገር መሆኑን መገንዘባቸው መልካም ነው። ነገር ግን የህን ለመገንዘብ አሥር ዓመት ሊወስድባቸው ባለተገባ ነበር... በሌለ አቅማቸው አርባ አራት ቦታ ከሚበጣጠሱ ሰብሰብ ብለው የኢሕአዴግ ጠላትነታቸውን በጋራ ሆነው ቢያራምዱት ይጠቅማቸዋል። ስለሆነም ግንባር መፍጠራቸው ለሕዝብም፣ ለኢሕአዴግም፣ ለእነሱም ጠቃሚ ነው የሚል ዕምነት አለኝ» ብሎ ነበር። ይህን ያለው በአንድ በኩል የተናገረው የማይከብደው ቀላል ሰው መሆኑን ሲያመለክት፣ በሌላ በኩል ግን አንዳንድ ድርጅቶች ሲያደርጉ የኖሩትን አስተዛዛቢ ድርጊት በፌዝ መልክ መናገሩ ነው። ***«የኅብረቱ መመሥረት ኢሕአዴግን ጨምሮ ለሕዝብም ይጠቅማል»*** ያለው ግን ዕውን ኅብረት ወደ አንድነት የሚያሸጋግር የመጀመሪያው እርከን መሆኑን አጥቶት ሳይሆን የተለመደ የአንድ ሰሞን የፖለቲካ ጨዋታ አድርጎ ስላየው ነበር፣ ይኸዉና ሆኖም እየታየ ነው።

ነገር ግን ገሀድ ዕውነታውን ክህደቱ የሸፈነበት እውር ትምክህተኛ መደፈር ብቻም ሳይሆን ከሕዝብ ጋር ሳይኖር አለሁ እያለ ራሱን ሲያታልል የኖረበትን መርዶ በይፋ የተረዳው በሰፊው ሕዝብ ዕመነት ላይ የተመሠረተው ቅንጅት አስተባብሮ ያዘመተው ኃይል ያሰማው የሰላማዊ ድምፅ ጩኸት መሸጎ የኖረበትን የመንደርተኛ ሠፈር ባልጠበቀው ሁኔታ አናግቶ በአናቱ ሊከነብለው መቃረቡን አይቶ ብርክ ከያዘውና በጭንቀት ከተዋጠ በኋላ ነው ደብቆ ያቆየውን የአውሬነት ባህርይ ይፋ አውጥቶ ሕዝብን በልቼ መጨረስ አለብኝ ብሎ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ያካሄደው።

ድሮውንም ቢሆን ባለፉት ዓመታት ከፈጸሚቸው የለየለት የጠላትነት ድርጊቶች አለመማር እንጅ ተፈጠሯዊ ሥነ - ባህሪያቸውን በማይገልጽ መጠሪያ ስም በከበሩት በእነበረከት ስምዖን የነበረን የማዕድ በረከት አሚጥጦ በመጨረስ ፍድፋዱን ለማጥፋትና ፀንቶ የኖረውን መሠረት ከሥሩ አናግቶ ለማፈራረስ እንጅ በነበረ እርሾ ላይ ሌላ በረከት ለማሳደርና ፀንቶ የኖረን መሠረት በበለጠ አጠናክሮ ለመቀጠል እንዳልዘመቱ ቁርጡን ያሳወቁን ገና ከመነሻቸው ጀምሮ ነበር።

በመሠረቱ ከዮሐንስ ክብረ - ምንግሥትንና ለክቡር ነገር በክብር ማለፍን፣ ከአሉላ ደግሞ የባህር በር ክብር ዘበኛነትን የመውረስ ዕድል የሌላቸው ክብረ - ቢስ ድሃዎች የጌቶቻቸውን ጫማ እየላሱና ሎሌ ሆነው እየተጎናበሱ መለመንን እንዳወቁበት ሁሉ በእኛ በወገኖቻቸው በወንድማማችነት መንፈስ መለመን ግን ውርደት መስሎ ስለታያቸው ሊያስቸግሩት ተዘጋጅተው ከዘመቱበት ሕዝብ ይልቅ ራሳቸውን በቀላሉ ከማይወጡበት ችግር ውስጥ ጥለው የበለጠ እየተቸገሩ መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ቆይቷል። የ15 ዓመት በክህደት የታጀበ የግፍ ወንጀላቸውን አንፃራዊ በሆነ አባባል ለማመልከት ያህል ውሃ ዋና የማያውቅ ሰው በጣዕር ተጨንቆ በመንፈራገጥ ላይ እንዳለ ሊያድነው የተጠጋውን ሰው ድንገት ቀድሞ የመያዝ ዕድል ካገኘ ከአናቱ ላይ ወጥቶ መላወሻ በማሳጣት የዳንኩ መስሎት ይዞት ለመስጠም የሚንፈራገጠው ከዚያ ወጭ ማሰብም ሆነ ማየት የሚችልበት ሌላ አማራጭ ስለሌለው ነው። የብሩኅ ተስፋ የለሽ የድድቅ ጨለማ ባለተስፈኞችም የዕለት ተዕለት ድርጊት በዚህ አባባል ሊገለፅ የሚችል እውነተኛ ስዕል ነው።

በእርግጥ የተቃዋሚ ኃሎች መቋጫ ውልና ተግባራዊ ለውጥ የሌለው ከንቱ መጯጯህ እርስ በርሳቸው ከመነካከስ አልፈው ለራሳቸው መናከሻ የሳሉትን ጥርስና ያዳበሩትን ልምድ የሁላቸውም ነካሽ በሆኑት የጋራ ጠላቶቻቸው ላይ ተባብረው አለማዋላቸው በበኩሉ በሕዝባዊ ትግሉ ላይ ከፍተኛ እንቅፋት የፈጠረ አፍራሽ ሚና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ተጫውቷል:: ጠላቶቻችንም ይህን መሰል ለእነሱ እንደአስቂኝ ቲያትር ለወገን ኃይል ግን አሳዛኝ ድርጊት የሆነውን በማየት «እንደእኛ እየሞተ የሚያሳይ ጠንካራ ተቃዋሚ እንፈልጋለን» ብለው በትምክህት መናገራቸው ራሱ በቂ ማረጋገጫ ይመስለኛል::

ተቃዋሚ ነን ባዮች ለብሔራዊ አንድነት ቆመናል እያሉ ወደ አገር ቤት ገብተው የህዝብን ችግር ለመቅረፍ ባይችሉም እንኳን በአንድነት አሰባስቦ ለሚያደራጅና ለሚያዘምት የኅብረት ግንባር ጥያቄ አንድ ወጥ ሁነኛ መልስ መስጠት አቅቷቸው 15 ዓመት ሙሉ ባሉበት ሲረግጡና «ቢከፋኛ ብመለስ» እያሉ የነገር ጠጠር ሲለቅሙ መኖራቸው ብቻ የማንነታቸው መታወቂያ ይመስለኛል:: በያሉበት እየተንከላወሱ በሀገር ህልውና ላይ እንዲህ ያለውን ጨዋታ እየተጫወቱ እንዲኖሩ ያደረጋቸው ትልቁ እንቅፋት ተቃዋሚ ነን በዮቹ በኅብረት ግንባር መሰባሰብን የሚፈልጉት የየራሳቸውን ድርጅት የበላይነት ለማሰፈን መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግላቸው እንጅ ኢትዮጵያን ለማዳን የታለመ ብቸኛ ዓላማም ሆነ ለዚህ ሃላፊነት የተዘጋጀ ኅሊና ኖሯቸው አልነበረም:: ስለሆነም በአሁኑ ወቅት በሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ስቃይና እልቂት የእነዚህ ሁሉ አፍራሽ ድርጊቶች ድምር ውጤት መሆኑ የሚያከራክር አይመስለኝም:: ከዚህም ሐቅ ውጭ ሌላ ሥውር ተዐምራዊ ኃይል ለጠላቶቻችን ያደረገው ነገር ኖሮ አይደለም::

እነዚህን ሁሉ መለስ ብየ እንድጠቃቅስ የተገደድኩት ከብዙ ዓመት የሜረኞች የነገር ፖለቲካ ይልቅ በወሮች ብቻ በሚቆጠር አጭር ጊዜ ውስጥ የተካሄደው የተቀናጀ ጥረት ምን ያህል ከፍተኛ ለውጥና ውጤት እንዳመጣ በሁለንተናዊ ትምህርት ሰጭነቱ ልንጠቀምበት እንደሚገባ አጠንክሬ ላሳስብ ስለፈለግሁ ነው:: ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የቅንጅት ዕድሜ በወሮች የሚቆጠር ቢሆንም በዋሳኝ ወቅት ተወልዶ ያለዕድሜው ለተጋረጡበት ችግሮች ሳይንበረከክ ፈተናውን ያለፈ የአይበገሬዎች ስብስብ ጠንካራ ድርጅት መሆኑን አረጋግጧል ብሎ መደምደም ይቻላል:: የአመራር አባላቱና ደጋፊዎቹ ታሥረው የሚሰቃዩትና በአደባባይ የሚረፈረፉትም የዓላማ ፅናታቸውና የአይበገሬ ወኔያቸው ያዘመታቸው ጀግኖች በመሆናቸው ነው:: አለበለዚያማ እንደሌሎች ማዶ ሆነው እያቅራሩ ቢቀመጡ ወይም አሜን ብለው ቢልመጠመጡ ኑሮ እሥራት ቀርቶ ግልምጫ እንኳ ባላረፈባቸውም ነበር::

እንደእኔ ግምጋሜ የቅንጅት አመራር የመጀመሪያውን ግንባር ቀደም ፈተና ይጠበቅበት ከነበረው በላይ በሆነ አኩሪ ድል ቢወጣም ሌላ ሁለተኛ ዙር ወሳኝ ፈተና እየጠበቀው ነው:: ፈተናው አንድም በየፈርጁ የሚፈታተኑትን ችግሮች እንደአመጣጣቸው እየመከተ በድል አድራጊነት የመወጣትና ለዋነኛው ግብ የመብቃት ብሥራት አለያም የዓላማ ጽናቱን፣ ሕዝባዊ ወገናዊነቱንና አይበገሬነቱን አሳይቶ ያለፈበት ፈተና በሌላ መልኩ ቀርቦለት ለማለፍ ባስቻሉት የኅሊና ዝግጁነትና የሞራል ጉልበት ሳያየው ቀርቶ የወደቀ እንደሁ ነው:: አያድርገው እንጅ እንዲህ ያለው ውድቀት ከመጣ አያይዞ የሚያመጣውን ሁለንተናዊ ውድቀትና ድቀት በቃላት ለመግለጽ በእጅጉ ይከብዳል::

በአጭሩ ግን ለወገኖቿ ጣፋጭ ብርቱካን፣ ለወገኖቿ ጠላቶች ግን የምትጎመዝዝ ሬት የሆነችባቸው እውነትም ዳግማዊት ጣይቱ *«መንፈስ ነው»* ብላ የሰየመችው ቅንጅት ስምን መልአክ ያወጣዋል እንደሚባለው በእርግጥም ስውን የማዳን መንፈሳዊ ተልዕኮ ያለው መንፈስ በመሆኑ በእህቴ ትርጉም ከልቤ እስማማለሁ:: ይሄም ሆኖ ቅንጅት የሰዎች ስብስብ የፖለቲካ ድርጅት በመሆኑ ፍፁምነት ሊጎድለው ይችል ይሆናል:: በዚህም ምክንያት አንድም እስከአሁን ጎልቶ ያልታየ ሰይጣን (በእርግጥም በአሁኑ ሰዓት ለይቶለት ጎልቶ እየወጣ ነው) በውስጡ ኖሮበት ከሰይጣኖቹ ጋር ወግኖ እንዳይጥለው አለበለዚያም የሰይጣኖችን ቅስም የመሥበር ኃይል ያለው ቅዱስ መንፈስ እንደሄዋን እባብ ለስልሰው በሚቀርቡት ሰይጣኖች ተሰልቦ እንዳይዎድቅ በጣም እሰጋለሁ::

ይሁን እንጅ ይህን ያደርጉ ይሆን በየ ከማልጠረጥራቸው ጀግኖች ለሚተናነቅላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳዩታል ብየ የምጠብቀው የአልበገር ባይ ጀግንነትን፣ ያስጨብጡታል ብየ የምጓጓው ደግሞ የአቸናፊነት ድል ብሥራትን እንጅ ሁላችንም



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ያልጠበቅነው መርዶንና ውርደትን እንደማይሆን ዕምነቴ ፅኑዕ ነው:: ሌላው ቢቀር ጣልነው ብለው ሊፎክሩ ከሚችሉት የሕዝብ ጠላቶች ያላነሰ በሕዝብ ዘንድ ሊያሳድር የሚችለው ጥላቻና ትዝብት መቸም ቢሆን መዘንጋት የሌለበት ይመስለኛል::

ይህን እንዲያደርግ ከሚገደድባቸው ብዙ የስጋት ነጥቦች:-

1. በአመራሩ ውስጥ የሚፈጠር መላላት፣
2. የወያኔዎች ወከባና ቡርቦራ
3. የቃልኪዳን ጌቶቻቸው የጨርሶ መግደያ ዲፕሎማሲያዊ ከበባ ይሆናሉ ብየ

ገምቻለሁ:: ከ15 ዓመታት ልምዳቸው እንደታየው የዎያኔዎች ትልቁ ጥበብና ስልት:-

- ተቃዋሚ ኃሎችን በፈጠራ ወንጀል እየከሰሱ ማዋከብና ሞራላቸውን ብቻም ሳይሆን ሕይዎታቸውን ጭምር በሚያመቻቸው የመግደያ ስልት እየገደሉ መቅበር፣
- በድርጅቶቻቸው ውስጥ ሠርጎ ገብቶ መከፋፈልና እርስበእርሳቸው እያዋጉ ማዳከም፣
- ከሚኗቸው እንዳይወጡና ከእጃቸው እንዳያመልጡ አድርገው ረግጠው በመያዝ እንደመሣሪያ እየፈቱና እየገጠሙ መጠቀም ... ወዘተ ናቸው::

እንደምገምተው የቅንጅት አመራር ተለቅመው የታሠሩት ከእነዚህ ሰይጣናዊ ቅንብሮች አንዱ እስኪሟላ ሊሆን ይችላል:: አፍራሽ ምክንያቶችንም እያየን ነው:: ይሄም ሆኖ ጠላቶቻችን የለመዱትን ፈጥነው ለማድረግ የሚችሉበትን ዕድል ያልሰጧቸውን የቅንጅት አመራርንና አብሯቸው የቆመውን ሕዝብ ከልብ አደንቃለሁ:: ወደፊትም እንደማይሰጧቸው ተስፋ አደርጋለሁ::

ሌለው የሥጋት ነጥቤ የሌላቸውን ስምና ክብር እየሰጡ አደላድለው ባስቀመጧቸው ጌቶቻቸው አማከኝነት የሚካሄደው የመሰንከያ ከበባ ነው:: የታጠቀ ሠራዊት አሰልፈው ሰላማዊውን ሕዝብ በመጨፍጨፍ ላይ ለሚገኙ ጎጠኛ የዘመኑ ፋሺስቶች ጎን ቆመው ተቃዋሚ ኃይሎች በምክር ቤቱ ቦታቸውን አለመያዛቸው አሳስቦናል እያሉ የሚለፍፉበት የማያሻማ ትርጉም አደላድለን ባሰቀመጠናቸው ዓላማ አስፈጻሚዎቻችን መልካም ፈቃድ የሚቸራችሁን አሜን ብላችሁ ተቀብላችሁ ኑሩ ነው:: ከዚህ ውጭ ሌላ ዴሞክራሲያዊ ግምትና ሰበዓዊ ትረጉም የለውም::

ሰሞኑን ቅንጅትን ጨርሶ ለማጥፋትና የአዲስ አበባን አስተዳደር ለወያኔ ቅጥረኞች ለማስረከብ የሚውጠነጠነው ሤራ ለአባባሌ በቂ ማረጋገጫ ይምስለኛል:: ጌታ የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል በመለኮታዊ ኃይሉ ፈቅዶ ደረገውን ከዘመኑ እኩያን ድርጊት ማነፃፀር ግድፈት መስሎ ካለታየ በስተቀር ድረጊቱ ለማነፃፀሪያነት ከታየ ግን ቅንጅትን ለማጥፋት በመካሄድ ላይ ያለው ባለበዙ መልክ የተቀነባበረ ሤራ ጌታን ለመገደል ከታቀደ እቅድና አፈፃፀም ጋር በማንኛውም መልኩ ሚመሳሰል ነው ማለት ይቻላል::

ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህራን በሕዝብ የሚወደደውን ጌታን በይፋ ለመግደል ከፍተኛ ሥጋት ስለነበረባቸው የማጥፊያ ዕቅዳቸውን የሚያቀነባብሩት በምኩራባቸው ውስጥ ተደብቀው ነበር:: ቅንጅትን ለማጠፋት የዘመቱ የወዳጅ መሰል ታሪካዊ ጠላቶቻችን ወኪሎች ደግሞ ትናንት ፊትለፊት ዘምተው ያጡትን ድል ለማሟላት የሚጥሩት ሌላወቹን የዘመኑን ይሁዳዎች በግቢያቸው እየኮለኮሉና ከርሳቸውን በዶላር እየሞሉ ነው::

በመሠረቱ ፈሪሳዊያንና የሙሴ ሕግ መምህራን ጌታን ለመግደል ያቀዱት የሚያሰገድል ወንጀል ኖሮበት ሳይሆን ሕዝብን ለማዳን የመጣ መሲህ በመሆኑ ባደረባቸው ሰይጣናዊ ተንኮል ተነሳስተው ነው:: ቅንጅትንም ተረባርበን እናጥፋው ብለው የዘመቱበት ሀገርና ሕዝብን የማዳን ዓላማና ነፃ አውጭ ፓረቲ ስለሆነ ነው:: ይሁዳ የመረጠውን ብቻም ሳይሆን የፈጠረውን ጌታን ክዶ እንደሸጠው ሁሉ በእኛም ሀገር የተከሰቱት የዘመኑ ይሁዳዎች ድምፅ ሆኖ ያስመረጣቸውንና አንጠላጥሎ ለዚህ ደረጃ ያበቃቸውን ቅንጅትንም ብቻ ሳይሆን ተወልደው ያደጉባትን እናት ሀገርና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ወልዶ ያሳደጋቸውን ሕዝብ ጭምር ከደው ከደመኛ ጥላቶቻቸው ጋር ግንባር ፈጥረው ለማጥፋት የዘመቱ ናቸው::

ይሁዳ በዕቅዳቸው መሠረት ጌታን ጠቁሞ ለማስያዝ ቀርቦ «ሰላም ለአንተ ይሁን» ብሎ እንደሳመው ሁሉ የእኛም አገር የዘመኑ ይሁዳዎች የሰላም መልዕክት ነው ብለው ሊነግሩን የሚፈልጉት የቅንጅትን የመግደያ ሜራ እንደሚያደነው አድረገው ነው:: ደግነቱ ግን ጌታ «ይሁዳ ሆይ የሰውን ልጅ በመሳም አሳለፈህ ትሰጣለህን?» እንዳለው ሁሉ የኢትዮጵያ በተለይም የአዲስ አበባ ሕዝብም ለተመሳሳይ ይሁዳዎች ተመሳሳይ መልስ እንደሚሰጣቸው እርግጠኛ ነኝ:: እነዚህ ሁሉ የሁለቱን ወገኖች የግብርም ሆነ የድርጊት ተመሳሳይነት ግልፅ አድርገው ያሳያሉ ብየ አምናለሁ:: ከአሁን በኋላ በጉጉት የሚጠበቁት ሁለት አይቀሬ ተዐምራዊ ክስተቶች ፈጥነው እንዲመጡ ነው:: የመጀመሪያው የቅንጅት ትንሣኤ ሲሆን፣ ሁለተኛው የይሁዳ ገመድ በቅንጅት ይሁዳዎች አነገት ላይ ውሎ ማየት ነው:: ይሄ ደግሞ የጊዜ ጉዳይ እንጅ አይቀሬ ሂደት ነው:: ከዚያ በኋላ የሺያጭ ገንዘቡ ብቻም ሳይሆን አሻሻጮቹም ጭምር እንደሚበተኑ ዕመነቴ ፀኑዕ ነው::

ስለዚህ የቅንጅት አመራር አባሎች እነዚህን ሁሉ ከእኔ በበለጠ ጠንቅቀው እንደሚያቋቸው ባውቅም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የበለጠ ማወቅ የበለጠ ሊያሳስትና ራስን ሊያስት እንደሚችል በብዙዎች ላይ ውሎ ስላየሁት የሚያልፍ ችግር የማያልፍ ታላቅ ስማችሁን እንዳይሠበረውና የማይደበዝዝ ክቡር ታሪካችሁን እንዳያሳድፈው በብዙ በምትጨነቁላት እናት አገራችንና ብዙ ችግሮችን በተጋፈጣችሁለት ወገናችሁ ስም እማፀናችኋለሁ::

## *ረ/ የተቀናጀ ሕዝባዊ ትግል ወሳኝነት*

***የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!*** በጽሑፌ ማጠቃለያ የማቀርበው የአንተን ሁለንተናዊ ሚናና ወሳኝነት የሚመለከት ነው:: ቀደም ሲል በጠቀስኳቸው ዋና ዋና የመንደርደሪያ ነጥቦች ባጭሩ ለማመልከት እንደሞከርኩት የሀገራችን የተወሳሰቡ ችግሮች የሚፈቱትና የአንተም ነፃነትና ክብር የሚመለሱት የጉዳዩ ባለቤትና ብቸኛ ተቻጋሪ የሆንከው አንተው አስተዛዛቢው ወቅት በአሳየህ አሳዛኝ ድረጊቶችና ባሰጨበጠህ ልምድ ላይ ተመሥርተህ ወዳጅና ጠላቶችህን አበጥረህ ስታውቅና በሕዝባዊ ኃይልነትህ ደግሞ በየፈርጁ ማካሄድ የሚገባህን ትግል በተቀናጀ መልኩ ስታካሂድ ነው:: ምክንያቱም አንተ ለሁሉም በሁሉም ሁሉም ነህና ነው:: ለሁለንተናዊ ሁለመናህ ከአንተ ፈቃድ ውጭ ማንም ገዥህ መሆን ቀርቶ ሞግዚትህ እንኳ ሊሆን አይችልም:: እስከአሁንም የሆኑት ሁሉ የሆኑብህ አጣጣዮችህ ስለበዙና በስምህ የሚካሄደው ንግድ ስለደራ ብቻ ነው::

በእርግጥ አንተም ራስህን በመጣልህና ቢያንስ እንኳን ትዝብት አይፈሬዎችን እሰከ አሁን ስታደርጉ በኖራችሁት ሁሉ የታዘብኳችሁ ስለሆነ ከአሁን በኋላ በቃችሁ አለማለትህ የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል:: ከአሁን በኋላ ግን ራስህን ራስህ አንስተህ በማቆም ከራስህ ላይ የወጡትን አሸቀንጥረህ ከእግርህ ሥር ጣላቸው:: አባባሌም ተምኔታዊ ሳይሆን በማድረግ ኃይልና ችሎታህ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ከኃይል ሚዛንህ ጋር ልታመዛዝነው ይገባል::

እንደምገምተው ቀላሎቹን አክብደህ ያየሃቸው በአንድ በኩል ካቅማቸው በላይ ግምት ስለሰጠሃቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ አቅልሎ መጣል የሚቻለውን ብርቱ ክንድህን ከፋፍለህ ስላዛልከው ነው:: ከዚህ ውጭ ሌላ ተዐምር በመካከሉ ጭራሽ የለም:: እነርሱ እነማንና ከይት የመጡ ናቸው? እኛስ ማንና ምን ሆንና ነው? እንዲህ የምንሆንላቸው? ብለህ ራስህን ጠይቀህ መልስ ካገኘህለት እስከ አሁን ተሰውሮብህ የቆይውን ዋነኛ የችግር መፍቻ ቁልፍ አግኝተህ መልሰህ በእጅህ አስገባህ ማለት ነው:: ይህ ቁልፍ ደግሞ የክብር ሥራ ማኅደርና የሞራል ሃብት፣ የወኔ ጉልበት፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሀገር ማዳኛ ፍቱን መድሃኒትና የነፃነት ሠንደቅ ...ወዘተ. ተቆልፈው የሚቀመጡበት መንበር ነው::

ስለተቀናጀ ሕዝባዊ ትግል ወሳኝነት የሌሎች አገሮች ልምድ ታክሎበት ቀርቶ የራሳችን የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት ብቻ በቂ ማረጋገጫ ነው:: የዘመናት ተጋድሎ ታሪካችንም ቢሆን በሕዝባዊ ተሳትፎ የተገነባ ነዉ:: ያ ግብታዊ የተባለለት የ66ቱ ሕዝባዊ አብዮት ተካሂዶ ለግማሽ ምዕተ- ዓመት ያህል ተደላድሎ የኖረውንና እንደ መልአክ ለመመለክ ተቃርቦ የነበረውን ንጉሣዊ አገዛዝ ገለብጦ በመጣል በአመራር ድክመት ተመልሶ ተናደ እንጅ አዲስ የሕዝባዊ አስተዳደር ሥርዓት መሠረት ተጥሎ በመገንባት ላይ ነበር::

በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ሕዝባዊ ትግል ግን እንደ የካቲቱ በግብታዊነት የሚካሄድ ሳይሆን የተቀናጀ ማዕከላዊ አመራር የሰጠና ወደፊትም የሚሰጥ ለአንተ በአንተ ከአንተ የተወለደ በአንተ ዙሪያ - ገብ እንክብካቤ የጎለበተ ቅንጅትን የመሰለ የፖለቲካ ድርጅት ያገኘህበት ወቅት ስለሆነ የተደቀኑበት ችግሮች የሚፈታተኑት ቢመስልም ትግሉን የበለጠ የሚያከረውና የድሉን ጊዜ የሚያፋጥነው እንጅ አፍኖ የሚያስቀረው ይሆናል የሚል ያየለ ስጋት የለብኝም:: ምክንያቱም ለሁለመናህ ወሳኝ ኃይል አንተ መሆንክን ባሰመርኩበት የአይበገሬ ኃያልነትህ መግለጫ ቃል ከተግባባን ዓይናችሁን ለአፈር እግራችሁን ለገደል የተባለባቸውን ሕዝባዊ መሠረትየለሽ ኑቁሎች ገፍተህ ለመጣል ከአንተ አቅም በላይ ሆነው የሚታዩበት የለየለት ጠላትነታቸው ብቻ መሆኑ ነው::

ይልቅዬ ችግሩ እነርሱ ከማንም የማይበልጡ እንበልጣለን ባይ ደካማነታቸውን የሸፈኑበት ልዩ ሰውነትና ጦርነት ፈጣሪነት ሳይሆን የለየለት ባንዳነትና ወገን መሰል ጠላትነት ነግሠው የመታገያውን መድረክ በመቆጣጠር የሚደረገውን ሕዝባዊ ጥረት ሁሉ እያመከኑ የማስቀረት ጠላትነታቸው የቀጠለ መሆኑ ነው:: እነዚህ ሁሉ ተደምረው ሲታዩ በአሁኑ ወቅት ያለውን የኃይል አሰላለፍ አስምሮ ለመለየት በእጅጉ ከባድና ውስብስብ አድርጎታል:: የሕዝቡንም የአንድነት ክንድ ለማዛል በመፈታተን ላይ ያለው ይኸዉ ነው:: በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ስም ሊያጠፏቸው የሚያሤሩትን፣ በስማቸው የሚነግዱትንና ክቡር መስዋዕትነት የሚከፍሉላቸውን እየለየን እናሥምርባቸው ቢባል የየራሳቸው መለያ ከሆነው ባህርይና ግብራቸው በስተቀር የሚሠመሩበት የተለየ ቀለም፣ የሚለዩበት የተለየ ቋንቋና የሚለኩበት የተለዩ የማኅበራዊ ኑሮ መሠረት የላቸውም:: በዚሁም ምክንያት ሕዝባዊ ትግሉ እነዚህ ሁሉ ባዕድ ጅምላ አጃቢዎች በተለያዩ አቅጣጫ ገብተው የሚያምሱት በመሆኑ ሁነኛ የቁርጥ ቀን የአገር ልጆችና የሕዝብ ወገኖች የሚያደርጉት ጥረትና የሚከፍሉት መስዋዕትነት ፈጥኖ አብቦ ለፍሬ የሚበቃበትን ጊዜ አራዝሞታል:: በቅድሚያ ወዳጅና ጠላቶችህን ለይተህ ማዎቅ አለብህ የምለውም ለዚህ ነው::

በአንድ ወቅት ለአጭር ጊዜ ትምህርታዊ ጉብኝት ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቸ ጋር ወደ ቻይና አገር ሄደን ነበር:: ገለፃ ያደርጉልን የነበሩት የፖለቲካ ሰዎች ሶቪዬት ኅብረትን (እንደዛሬው ሳትሆን ማለት ነው) ሶሻል ኢምፔሪሊስት ናት እያሉ ያጥላሉ ስለነበር ለምን ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ:- «ኢምፔሪያሊዝም በራሱ ቅራኔ የሚወድቅ ሥረዓት ሲሆን፣ ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም ግን በአሳሳች ባህሪው ሶሻሊዝምን የሚበርዝና በሌሎች ሀገሮች የሚካሄዱትን ታዳጊ አብዮቶች የሚሰነክል ነው::» ያሉትን አስታውሳለሁ:: የኢትዮጵያም ሕዝብ ትግል ወደፊት የሚጠብቀው ግራ አጋቢ ተፈታታኝ ችግር ይኸው ሳይሆን እንደማይቀር እርግጠኛ ነኝ:: ከወዲሁ ወዳጅና ጠላቶችን መለዬት ወሳኝ የሚያደርገውም ይኸዉ ነው::

በእርግጥ የሰውን ልጅ የልቡን ከህደትም ሆነ የዕምነቱን ፅኑነት ከፈጣሪው ወጭ መርምሮ እንዲህ ያለ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይመስለኝም:: ይሄም ሆኖ ማንነቱን የሚያጋልጡበት ብዙ ገጠመኞች እንደ ጥላው እየተከተሉ አብረውት ስለሚኖሩ እሱነቱን ለመለየት ረጅም ጊዜ አይወስድም የሚል ግምት አለኝ:: በተለይም ይህ ወቅት የሁሉም ማሳያ፣ ማታያያና መተዛዘቢያ ወቅት ስለሆነ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የመጨረሻው ይሆናል ባይባልም ሰው አዳኝ የሆኑ ሰዎችህንና ሰው ገዳይ ሰዎችህ ነን ባይ ወገን መሰል ጠላቶችህን ግልፅ አድርጎ ያሳዩህ ይመስለኛል፡፡

ስለዚህ በእንደዚህ ያለው የማንነት መግለጫ በሆነው አስተዛዛቢ ወቅት በውል ለይተህ ላወቀሃቸው አካሎችህ በብርቱ ልትጠነቀቅላቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ካለብህ የሰው ድህነት የምታገግመው ያሉህን ቆጥበህና ጠብቀህ ስትጠቀምባቸው እንጅ አጋልጠህ ስተሰጣቸውና ጨርሰህ ስታጣቸው አይደለም፡፡ ይህን ስል ሰው በተፈጥሮው ፈፅም ባለመሆኑ ሰዎችህን ልታምናቸው እንጅ ፍፁም አድርገህ ልታያቸው አይገባም፡፡ ምክንያቱም ሰዎቼ ናቸው ያልካቸውና ሰዎችህ ነን ያሉህ ሁሉ ሰዎችህ ሆነው አልዘለቁምና ነው፡፡

በድሮው ሃይማኖቱ ጥብቅ፣ ስርዓቱ ክቡር፣ ባህሉ ተወዳጅ በነበረበት ዘመን ሁለት ለትዳር የተሳሰቡ ፍቅረኞች ተገናኝተው ሀሳባቸውን ለመገላለፅ የሚችሉበት ቦታና አጋጣሚ ስላጡ ወንድየው ለሴቷ ፍቀረኛዉ መገናኘት የሚችሉበትን ቀን ጠይቋት እንዲመጣ ጓደኛውን ይልክባታል፡፡ እርሷም ሚስጥሩ ከሁለቱ የሚስጥር ሙዳይ ወጥቶ ወደ ሦስተኛ ሰው መሸጋገሩ ቅር ስላሰኛት፡-

«ከሆነም ይሆናል፣ ካልሆነም አይሆንም፣
ምንም ታቦት ቢሆን፣ ሰው መላክ አይሆንም፡፡»

ብላ መልስ ላከችበት ይባላል፡፡ ስለዚህ ሰዎችህ ታቦቶችህ ሊሆኑ ይችላሉ፣ መላዕክቶችህ ግን ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ከአንተ በላይ ሰው ሆኖ ሰው የሚያደርግህ ፍፁም ሰው የለምና ነው፡፡

በዳዊት መዝሙር ስለሰው ልጅ አፈጣጠርና ክብር እንዲህ የሚሉ መንፈሳዊ ቃላት እናገኛለን፡-

4. «ለሰው ይህን ያህል የምታስብለትና የምትጨነቅለት ለምን እንደሆነ ይገርመኛል፣
5. ከመላዕክት በጥቂቱ ብታሳንሰውም የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት
6. በፈጠርካቸው ፍጥረቶች ሁሉ ላይ ገዥ አድርገህ ሾምከው» የሚል ነው፡፡

እንዲህ ያለውን ወሰን የሌለበት ሥልጣን፣ ክብርና ሀብት ሰጥቶ የፈጠረው አምልክ ለምን አንዲት ትንሽ ነገር እንዳጎደለበት አይገባኝም፡፡ ይኸውም አልጠግብ ባይ እራስ ወዳድነት ነው፡፡ ልዑል እግዚአብሔር እራሱን ሳይወድ በራሱ አካልና አምሳል የፈጠረው ታላቁ ፍጡር ትንሽ አድርጎ የሚያሳዩውን ራስ ወዳድነት ከየት እንዳመጣው ባለማወቅ ከፈጠረው አምላክ የበለጠ ራሱን እያመለከ መኖሩን ቀጥሎበታል፡፡ እንዲህ ያለው የአጥንት በሽታ ተጋቦት ደግሞ እንደእምነታችን ጽናት፣ እንደ ማኅበራዊ ኑሮአችን ዕድገትና እንደ ንቃተ - ኅሊናችን የአድማስ ስፋት በዓይነትም ሆነ በመጠን ይበላለጥ እንጅ እገሌ ተገሌ ሳይባል ሁሉንም ሥጋ ለባሽ የበከለና የሚበክል ችግር ይመስለኛል፡፡

አዳምና ሄዋን የገነትን ምግብ እየበሉና ምድራዊ ፍጥረታትን ሁሉ እያስገበሩ በገነት እንዲኖሩ ካደረጋቸው አምላክ ተዕዛዝ ይልቅ ለምንስ አንዲት ነገረኛ ዛፍ ትቀርባችኋለች ብሎ የነገራቸውን ጠላት የበለጠ አምነው ባመጡት ጣጣ በወራሽ ልጆቻቸው ላይ ነገርተኛነትን ዘርተው እንዲያልፉ አድርጓቸዋል፡፡ ውሎ ሳያድር ወንድም ወንድሙን እንዴት እንደሚገድል አስተምሮ ያለፈው ቃኤል ደግሞ ወንድሙን አቤልን የገደለው በራስ ወዳድነት ነው፡፡ አልያማ ዛሬ 6.5 ቢሊዮን ሕዝብ የተሸከመችው ምድር በዚያን ወቅት ለአዳምና ለልጆቹ ጠባቻው አልነበረም፡፡ እንደእኔስ ውስን ግንዛቤ ዓለም የምትጠበውና የሰው ልጅ የሚጠፋፋው ራሱ የፈጠረውን የራስ ወዳድነት ልክፍት ወይም ትምክህት በሚያመጣው የባህሪ ክፋትና የስልጣኔ ጎጅ ጎኖች ከሆኑት ለምሳሌም፡- በአንዱ ሰው መሆንን እየጠሉና እየጣሉ ወደእንስሳነት የመለወጥ ፆታ - ቢስነት እንጅ በሕዝብ ቁጥር ብዛት አይመስለኝም፡፡ ውሃን ወይን ያደረገና የገነትን ምግብ ለሰው ልጅ የመገበ አምላክ ምድርን ደጋግማ እንድታፈራ ማድረግ የሚሳነው አይመስለኝም፡፡ ጌታም በወንጌል «በራሳቸው ዓይን ላይ ያለውን ወፍራም ግንድ ሳያዩ የሌላውን የዓይን ጉድፍ እናንሳልህ ይላሉ»



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ያለውም የሰው ልጅ ራሱን እንዳያይ የሚያደርግ የራስ ወዳድነት ባሽታ ያለበት መሆኑን በልበአምላክነቱ መርምሮ ያወቀብንን ድህነት አጋልጦ ሲያሳየን ይመስለኛል።

በአጠቃላይ አጥብቀው የወደዱትና ጠፍንገው የያዙት ራስ ወዳድነት ከመጠን ሲያልፍ ከራስ ላይ ወጥቶ ራስ እንደሚያዞርና የሚያደርጉትን አሳጥቶ አሽቀንጥሮ እንደሚጥል አወዳደቃቸው ከከፋና ስምና መቃብራቸው ከጠፋ በዙ ሰዎች ታሪክ ማረጋገጥ ይቻላል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ - ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ የሞአ አንበሳ ዘ እምነገደ ይሁዳ ዘውድ ከልጅ ልጆቻቸው ሳይወጣ ለዘላለም ፀንቶ እንዲኖር የሚደነግግ ሕገ - መንግሥት ነበራቸው። ይህንን ያሉት ከአልጋ ወራሽነት እስከ ንጉሠ - ነገሥትነት ምን እያደረጉ እንደተንጠላጠሉ መለስ ብለው ባለማዘከር ይመስለኛል። አለበለዚያማ ንጉሠ - ነግሥትነቱን የወሰዱት ከአፄ ምኒልክ ልጆች እንጅ ከራሥ መኮንን አልነበረምና ነው። እንደዚያ የተባለለት ሕገ - መንግሥት ግን ወደ ልጅ ልጆቻቸው መተላለፍ ቀርቶ ራሳቸውን እንኳ በወጉ እንዲያልፉና በክብር እንዲያርፉ ሊያደርግ አልቻለም። ምክንያቱም ሌሎችን ለማጥፋት የተጠቀሙበት የነ አነር ምክርና መርፌ በራሳቸው ላይ ያዘነበለ ጊዜን ደግፎ ለማቆምም ሆነ ጊዜ ያደላላቸውን ጊዜያዊዎች ወግቶ ለመግደል አላስቻለምና ነው።

ኮሎኔል መንግሥቱም ቢሆኑ ምንም እንኳን በንጉሡ ላይ የፈፀምኩት ሁሉ በእኔም ይደርሳል የሚል ስጋት ባይኖርባቸውም እንደሰው ቆመው መዋላቸውንና ትናንት የተናገሩትን ከዛሬው ጋር እያላተሙ ማውገርገራቸውን ብቻ የተሚላ ትርጉም እንዳለው ሕይወት የሚቆጥሩት ካልሆነ በስተቀር ሩጠው የማያመልጧትና በአንደበተ ጮሌነት ሞግተው የማይረቷት ያች መግነዝ መጥታ እንደሰውነታቸው ሲያልፉ በእናት አገራቸው የሚቆም ሃውልት ቀርቶ የሚተከል ምልክት እንኳን የማይኖራቸው ዘላለማዊ የባዕድ አገር ሚች መሆናቸው የሚያጠያይቅ አልሆነም።

እርሳቸው በምን እንደሚተረጉሙት ባላውቅም እኔ ግን ስለእርሳቸው ባሰታወስኩ ቁጥር አዝንላቸዋለሁ። ምክንያቱም እንደ ሌሎቹ የነጋሲነት ዘር ቆጥሬ ለዚህ የበቃሁ ነኝ የማይሉ እንደኛው ተራ ሰው ሳያስቡ ከደረሱበት የአገር መሪነት ክብርና ማዕረግ ይልቅ ለተነሱበት ትንሽነት አድልተው አወዳደቃቸውን በማክፋታቸውና ክብራቸውን ራሳቸው አውረደው በመጣላቸው ነው። የተናገሩትን ያህል ሆነውና በተናገሩበት ቦታ ቆመው አልፈው ቢሆን ኖሮ ግን ስማቸውን ሲጠሯቸው ከነበሩት ባለክቡር ታሪክ ሕያው መሪዎች አንዱ ለመሆን በበቁም ነበር። በእርግጥ በዚያ ማንነትን በሚፈታተን ጭንቀት ውስጥ ሆነው ይሄ ሁሉ ላይታያቸው ይችላል። ፈሪና ንፉግ እያደር ይቀረቁረዋል እንደሚባለው ካለፈ በኋላ መለስ ብለው ሲያስቡት ግን ሳይቆጫቸው አይቀርም ብየ እገምታለሁ።

የዛሬዎቹ ደግሞ የባሰውኑ ሳያስፈልግ እየዋኙ የመጡበትን ያቋተ የንፁህ ሕዝብ ነፁህ ደም እንዲከፍሉ መገደዳቸው አይቀሬ ሂደት ነው። ምክንያቱም በዝናብ ወይም በመስኖ ውሃ እንጅ በደም መስኖ ዘርቶ ያበቀለና አምርቶ የተጠቀመ የለምና ነው።

የደርግ ከፍተኛው ወንጀል መገደል ከሚገባቸው አገር ገዳይ ወንጀለኞች ጋር አገር ለማዳን የተሰለፉ ውድ የሀገሪቱ ልጆችን አብሮ መግደሉ ነው። የዛሬዎቹ ደግሞ ሰዎችን ብቻም ሳይሆን የሰዎች መፈጠሪያ ሆና የኖረችውን ሰው መርጦ ወላጅ እናት አገር አጥፍተን ሰው የሆኑ ሰዎች ዳግመኛ እንዳይፈጠሩ እናድርግ ብለው የዘመቱ በመሆናቸው ምን ሊባሉ እንደሚገባ የቋንቋ ባለሙያዎች እንዲያተኩሩበት በዚህ አጋጣሚ አሳስቤ አልፋለሁ። እኔ ግን እንደኛው ሰው የመሆናቸውን ክብር ሳይነካ ከክህደታቸው ማተብ የለሽነት፣ ከባህሪያቸው ክፋትና ከጭካኔያቸው አረመኔያዊ ድረጊታቸው አኳያ ሳገናዝበው ግብረ - አራዊት ቢባሉ ይስማማቸዋል ብየ አምናለሁ። እንደሚታወቀው አውሬ ያየውን ሁሉ መግደል አለብኝ በሎ የሚራወጠው ዕውን ያን ሁሉ በልቶ ለመጨረስ ሳይሆን መግደልና ማጥፋት የተፈጥሮ በህሪው ስለሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ እነርሱም ከዚህ የተለዩ አይደሉም ብየ ብደመድመው አጋንኘ ያቀረብኩት አይመስለኝም።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በእርግጥ እነርሱም ቢሆኑ በዚህ አረመኔያዊ ድርጊታቸው ገፍተው ዳር እንደማይዘልቁና ካሰቡት ግብ ላይ እንደማይደርሱ ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ሰይጣናዊ አምልኮታቸው ግን እያፈራረስን እንኖራለን፣ እየገደልን እንገዛለን ሳይሆን አጥፍተን እንጠፋለን የሚባልለት መሆኑ በይፋ ከታየ 15 ዓመቱን አስቆጥሯል፡፡ የነጥቡ መደምደሚያ እነረሱ አንኖርም ብለው የማያኖራቸውን ሲሠሩ አንተ የመኖር ዕድልና የሚኖሩበት ዕድሜ የምትሰጣቸው ለምንድነው? የሚለው ነው፡፡

መልካም አጋጣሚ መልካምነቱን የገለጠበት ጊዜ ካለፈ ተመልሶ የመገኘት ዕድሉ በጣም የጠበበና የራቀ ነው፡፡ በወቅቱ ያልሰበሰቡትን አዝመራ ከረገፈ በኋላ ለመሰብሰብ መሄድ ደርቆ በቆመ አካሉ እየተወጉ ለመቁሰልና ደም ለማፍሰስ እንጅ ምርት ለማፈስ እንደማይቻል ሁሉ የመልካም አጋጣሚ የድል ፍሬም እንደዚሁ ነው፡፡ በአለፉት ዓመታት በዙ መልካም አጋጣሚዎች ተገጣጥመው በአግባቡ የተጠቀመባቸው ባለመኖሩ ውጤታቸው የተገላቢጦሽ ሆኖ ሊጠቅሙ የመጡለትን ተጠቃሚ ሕዝብ ተጎጅ እንዲሆን አድርገውት አልፈዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የሚታየው የአገጠጠ ችግር የእነዚህ ሁሉ ድክመቶች ድምር ውጤት ነው፡፡

እንደ እኔ ግምጋሜ የአሁኑ ወቅት መልካም አጋጣሚ ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የመጣ ነው በየ እገምታለሁ፡፡ እንዲያውም የእግዚአብሔር ፈቃድ የታከለበት ነው ብየ ብናገር ብዙ ደጋፊ መረጃዎች ስላሉ በአጉል ተስፈኝነት የተነገረ ነው የሚያሰኝ አይሆንም፡፡ ከመረጃዎቻ አንዱ *«እግዚአብሔር እስራኤሎችን ማዳን ስለፈለገ በጠላቶቻቸው እንዲጨከንባቸው አደረገ»* የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በአሁኑ ወቅት በአንተ ላይ ከሚፈፀመው ግፍና በደል አንፃር ሳገናዝበው ሊያድንህ ፈልጎ ያደረገው እንጅ ሊያጠፋህ ወስኖ እንዳልሆነ ጽኑዕ ዕምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ያለው መልካም አጋጣሚ በቸልተኝነት መታለፍ የለበትም፡፡ እንዳለፈው ሁሉ ይህንንም ያለውጤት ካሳለፍነው ግን እስከመጨረሻው ሲለፋ የሚኖር እንጅ የሚያልፍለት ይኖራል ብሎ ለመተንበይ በእጅጉ ይከብዳል፡፡

እንደሚታወቀው የአገር ጉዳይ የሁለመና ጉዳይ ነው፡፡ ሁለመና ማለት ደግሞ የነበረን፣ ያለንና ወደፊትም ሊኖር የሚገባውን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ የሁለመናችን ሁለመና በመሆኑ በክብር ተወልዶ በክብር ያደጉባትን፣ ለወግ ለማዕረግ የበቁባትንና በክብር የሚያልፉባትን እናት አገር ማጣት የሰውን ልጅ ክቡር ፍጡርነት ጠንቅቀው ለሚያውቁ ሰዎች መግለጫ ቃላት የማያገኙለት መሪር ሐዘን ነው፡፡ የሰውነትን ሁለንተናዊ ክብር አሳጥቶ ከሁለንተናዊ ድህነት ላይ የሚጥል ከባድ ምድራዊ ፈተናም ነው፡፡

በእርግጥ ቅርፀ ሰውነታቸውን ሳይጨምር ሰው የሚያሰኝ ሰውነታቸውን ለጠሉና ለጣሉ መኖ አዳኝ በየደረሱበት ሆዴ አገሬ ለሆኑ ሰው መሰል እንስሳዎች ግን ትርጉም የለሽ መሆኑን ያለፉት ዓመታት ተመክሮዎች አስተምረውኛል፡፡ እንደእኔ ቅን ኅሊና ኢትዮጵየዊ ስደተኛ ሲባል የሀገርና የወገን ፍቅር ረሃብ ያጠቃቸው ችግረኞችና የደም እንባ እያለቀሱ የሚኖሩ ሐዘንተኞች መስለው ይታዩኝ ነበር፡፡ ለካስ ቅጹን ሞልተው ኬላውን እስከሚያለፉ እንጅ ከዚያ በኋላ በውስጡ ብዙ ውጥንቅጣቸው የወጣ መጢቃዎችና የአገር ሰላም ማጣትና የወገን እልቂት መልካም አጋጣሚ የሆነላቸው አንጡራ ባዕዶች የሚነግዱበት የደራ ገበያ መሆኑን ያወቅሁት ዘግይቸ ነው፡፡ ተወልደው ያደጉባትን እናት አገር መለስ ብለው ሊያስቧት ቀርቶ በስሟ ለመጠራት እንኳ የሚያፍሩባት የእንግዴ ልጆችም ቀጥር ቀላል አይደለም፡፡

እነዚህ ሁሉ የትውልድ አፈሪያቶች ዘወትር የሚጣደፉት አገር ጎብኝ ቱሪስት ሆነው ሄደው ከዚያ ጠላቶቹ ከሚያምሱትና ችግር ካጎሳቆለው ሕዝብ መሃል የተለዩ ሰዎች መስለው ለመታየትና የአገሪቱ መሠረት እየተናጋ መሆኑን በግልፅ እያዩ እራሳቸውን ብቻ አደላድሎ ለማኖር የሚያስችል ኑሮ ለማደራጀት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሁኔታው ሲገመገም አበዛኛው ስደተኛ ነኝ ባይ አሰደዱኝ ከሚሏቸው ከአገር የመውጫ ምክንያት ጠላቶች ይልቅ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ነቅለው እንዳሰደዷቸው አድርገው የሚያዩና አምርረው የሚጠሉ ናቸው ከሚያሰኝ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስገድድ ሆኗል። ከሁሉም በላይ በእጅጉ የሚያሳዝነው ደግሞ የአገር ጉዳይ ቀጥተኛ ትርጉሙንና ተገቢ ክብርና ማዕረጉን ፈፅሞ አጥቶ መነገጃ ሸቀጥ ሆኖ ሲቸረቸርና የፈረንጅ አገር ኑሮ ማደላደያ መደላድል ሆኖ ሲያደላድል መኖሩ ነው። የፖለቲካው መድረክ ፈቃድ የማይጠየቅበትና ገብር የማይከፈልበት ነፃ የመገባባያ መድረክ በመሆኑ ለአገር የሚውል የውል ሰው መሆን ቀርቶ ራሱን እንኳን በወጉ ማዋል የማይችለው ሁሉ በመሰለው እየተረጎመ መጫዎቻ እንዳደረጋት ከብዙ አጋጣሚዎች መገንዘብ ይቻላል።

የአንዳንዶቹማ ቀደምት ነን ባይ ፖለቲከኞች የፖለቲካ ቲያትር ከእነዚህ ሁሉ የባሰ አስተዛዛቢ ሆኗል። ትናንት በቃላት ደረጃ ሲያካሂዱት ለነበረው የውጊያ ግንባር ቀደምት ነን ሲሉ እንዳልኖሩ ሁሉ ዛሬ ደግሞ ለሰላማዊ ትግሉ ግንባር ቀድሞ ተዋናይ በመሆን ቀድመው ተኮልኩለው እየታዩ ናቸው። ድሮውንም ቢሆን እነርሱን ለሚያደላድል የነገር ጦርነት እንጅ የአገር ክብርን ለማስከበር ሲባል ይካሄድ ለነበረ የጦርነት ጎራ አዋጊዎች አልነበሩም። የእነርሱ የዘወትር ጥረት በስምህ እየነገዱ የጥሪት ቋታቸውን ከመሙላት ባለፈ እውን ችግርህን ተጋርተው እንደአንተው አብረው ለመቁሰልና ለመድማት ቀርቶ ስትቆስል እንኳ ላለማየት አያሳየን ብለው እርቀው ከሄዱ በዙ ዓመታትን አስቆጥረዋል። አንተን የሚፈልጉህና የሚቀርቡህ በአባይ ምላሳቸውና በመንጠቂያ እጃቸው ብቻ መሆኑን የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የወቅቱ ጥድፊያቸው የአንተና የእናት አገርህ ችግር እየሰፋና እየከፋ መምጣት ሳይሆን ያችን በሰለጠኑባት የሤራ ልምድ ተከላክለውና በተካኑበት አስመሳይነት አታልለው የማያመልጧትን ጥሪ ያስከተለችው ጀንበር ልታመልጣቸው መቃረቧን ስለሚያውቁ የት እንወድቃለን የሚለዉ ስጋት ስላስጨነቃቸው ነው። ለዚህ ጭንቀታቸው ያገኙት የማሰተዛዘኛ መልስ እድሜ ልካቸውን እየጋጡ ሲያራቁቷት ኑረው ጨርሰን እናጥፋት ብለው ለዘመቱባት ጠላቶቿ አሳልፈው የሰጧትን የብዙ እደኞች እዳ ተሸካሚ የሆነች ችግረኛ አገር መውደቂያ ያጣ ጥንባቸውን እንድትሸከምላቸው ለማድረግ ነው። ስለሰላማዊ ትግል በየቦታው ሲያቃጭሉ የከረሙትና እስከአሁን ተናግረውት የማያውቁትን የቃላት ጋጋታ የሚያወርዱበት ምክንያት ሰምና ወርቅም የእቅዳቸውን ቅድመ ሁኔታ ለማመቻቸት መሆኑ አላጠራጠረኝም።

ከገሃድ እውነታዎች ጋር ራሳቸውን አስተዋውቀው የማያውቁት ግብዞች በሰላማዊ ትግል ሺፋን ወደ አገር ቤት ለመግባት ሲወስኑ ትናንት እያደረግን ነው ይሉዋቸው ለነበሩት ሁሉ በቅድሚያ መልስ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያሰቡበት አይመስለኝም። ሌላው ቢቀር በሰላማዊ ትግል ሺፋን ራሳቸውን ብቻ አሾልከው ለማስገባት ሲዘጋጁ አለን ሲሉ የኖሩትን ሠራዊት የት እንዳደረሱት የታወቀ ነገር የለም። በእርግጥ ሕዝብን የማታለል ችግር የሌለባቸው ልማደኞች አንድም ከወያኔዎች ጋር የመከላከያ ስምምነት አድርገን ቀላቅለነዋል፣ አሊያም ወያኔዎች ሰላማዊ ትግሉን ቢያደናቅፉ እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ ሆኖ ተከታይ ትዕዛዛችን እየተጠባበቀ ነው ይላሉ እንጅ አይ ከድሮውም አልነበረንም እንደማይሉ፣ ባይሉንም አስቀድሞም የታወቀ ቋሚ መልሳቸው ነው።

በጥቅሉ ከእንደዚህ ያለው ኢትዮጵየዊ ሃላፊነት ከጎደለው ቲያትር የምናገኘው ትልቅ የእንቆቅልሽ ጨዋታ ሁሉንም እንሆናለን ሲሉ ኖረው ምኑንም ሳይሆኑ በመቅረታቸው የደረሰባቸውን በቃላት ጥሬ ካብ የማይከላከሉት የቁም ሞት መልሶ ሕይዎት እንዲዘራ ለማድረግ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች ከችግሩ ጋር ፊት ለፊት እየተጋፈጡና ከጠላት ጋር ተናንቀው እየወደቁ ያስገኙትን ድል በሰላማዊ ግንባር ፈጠራ ሺፋን ተጠልለው ገብተው ለመቀላወጥ፣ ከቻሉም በተለመደ ቀሳጢነታቸው የእኛ ብቻ ጥረት ውጤት ነው ብለው ለመንጠቅ መሆኑን አዝማሚያው ግልፅ አድርጎ እያሳዩ ይመስለኛል።

እነዚህን ሁሉ ገሃድ እዉነታዎች በመንደርደሪያነት የገለፅኩልህ የበለጠ ሐዘን እንዲሰማህ ፈልጌ ሳይሆን በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ንኝ ባይ ሁሉ ቁም ነገር የሚሞላና ለውጤት የሚበቃ ተግባራዊ ሥራ ሠርቶ ነፃ ያወጣኛል ብለህ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ራስህን እንዳታዘናጋ በግልፅ አሳየቼ አንተን ነፃ የምታወጣው አንተው ራስህ በመሆንህ ራስህን እንድታዘጋጅ ለማሳሰብ ነው:: ይህ ባይሆንማ ኖሮ ለረጅም ዓመታት ሲለቀለቅ የኖረው የወረቀት ክምርና እየተመረጠ ሲንከባለል የኖረው የቃላት ናዳ ጠላቶችህን ደፍጥጦ ድራሻቸውን በማጥፋት ነፃ ሊያወጣህ በቻለም ነበር:: ይሁን እንጅ በስምህ እየነገዱና በችግርህ እየተጫወቱ ከመኖር አላለፉም:: ይህን ሲያደርጉ የኖሩ ግብዞች ጭንቀት የአንተ ስቃይና እልቂት ሳይሆን የጣዖቶቻቸው እየተናዱ መሄድና ወደ መቃብር መውረድ ብቻ ነው:: እኔ እንደህግ ምሥክር ቃል ሆኖ እንዲዎሰድልኝ በምፈልገው አስተያየት እየታገልንልህ ነው እያሉ በመሸንገያ ቃላት ብቻ ያበሰሉትን የወረቀት መና ሲመግቡህ ከኖሩት የፖለቲካ ደላላዎች ይልቅ የሌሎቹ አገር ሰዎች ለአገራቸው በማድረግ ላይ ያሉት ትንቅንቅ ትምህርት ሊሰጥህ ይችላል ብየ እገምታለሁ::

ይህን ስል የሁለመናቸውን አትኩሮት ለአንተ ሰጥተው አእምሮአቸውን እየጨመቁና በገንዘባቸው እየደሙ ሌት ተቀን ትግልህን ለማገዝ የሚጥሩና የሚግሩ እንዳሉም ጠንቅቄ አውቃለሁ:: የበረዶ ግግርና የፀሐይ ሐሩር ሳይበግራቸው ሌት ተቀን በሰልፍ እየወጡ ድምፅህን ወክለው በዓለም አደባባይ የሚጮሁልህንና ሻማ እያበሩ በድል አድራጊነት የመውጣት ተስፋህ ብርሃን ሰጭ ሆነው የሚታገሉልህን ኢትዮጵያውያን ሁሉ አደንቃለሁ:: እንዲያውም መቸም ቢሆን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ባለማሰለስ እንዲህ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚደረገው ትግል እጅግ የሚያስደንቅና ይበል የሚባልለት ተጋድሎ ነው:: ነገር ግን በአንድ በኩል ከቁጥር አኳያ ሲታይ በኢትዮጵያዊነት ስም የሚጠራውና ለኢትዮጵያዊነቱ የሚዋደቀው ስንቱ እጅ ነው የሚለው ጥያቄ ሲነሳ መልሱ እጅግ የሚያሳዝን ይሆናል:: እንዲያውም የአገር ጉዳይ ሲነሳ እንደእሬት የሚመራቸው የትውልድ አረሞች ቁጥር ቀላል አይደለም::

በሌላ በኩል ደግሞ ከብሔራዊ ችግራችን የቅራኔ አፈታት ህግ አኳያ ከታየ ወሳኙ የውስጥ ትግሉን ማጠናከሩ ላይ ነው:: ይኸውም ማለት የችግርህ መፍቻ ቁልፉ አንተ ነህ ማለት ነው:: የአንተ የሆነው የውጪው ኃይል አንተ ለምታራመደው የነፃነት ትግል ድጋፍ ሰጭ እንጅ አንተን ተክቶ የአንተን ወሳኝ ሚና የሚጫዎትና ከአንተ ጎን ተሰልፎ ፊት ለፊት የሚጋፈጥ አይደለም:: ላድርግም ቢል ሁኔታው አይፈቅድለትም:: በሌላ አባባል መድፈኛ ጦር ወደ ግብ ከማቃረብ አልፎ እግረኛ ጦርን በመተካት ግብ መያዝ እንደማይችል ሁሉ የአንተንና የድጋፍ ሰጭህን ኃይል አሰላለፍ ማየት ያለብህ ከዚህ አንፃር ነው::

በአሁኑ ወቅት በማካሄድ ላይ ያለኸው ትግል ከፍተኛ እምርታ እንዳሳየ ባስመዘገብከው ውጤት ተረጋግጧል:: እንዲህ ያለው ሁለንተናዊ ዝግጅት ባለብዙ ፈርጅ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ከዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ከፍተኛ ተጋድሎ ላደረጉት የቅንጅት ኃይሎች ያለኝን አክብሮትና አድናቆት በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እወዳለሁ:: ይህችን መልዕክት የጻፍኩበት ዓላማም የእስካሁኑ ተጋድሎህ ከዚህ ደረጃ ላይ ካደረሰህ ወደፊት ደግሞ ምን ማድረግ እንደሚገባህ ያለኝን ልምድ ለማካፈል ነው::

በእርግጥ ከዚህ ከፍተኛ ውጤት ላይ ለመድረስ ብዙ ወጣት ልጆችህና ኮትኩተህ አሳድገህ ለከፍተኛ ሃላፊነት ያዘጋጀኻቸው ምሑሮችህ በአደባባይ ተጨፍጭፈዋል:: የአካል ጉዳት የደረሰባቸውና ማኅበራዊ ኑሮአቸው የተናጋው ቁጥር ደግሞ በእጥፍ ድርብ የበዛ ነው:: ይህም ሁሉ እየሆነብህ በታላቁ ትዕግሥትህ ያከማቸኸው ምሬት ስለገነፈለ ሕዝባዊ ድምፅህን መሣሪያ አድርገህ በወሰድከው እርምጃ ጠላቶቻችን በሰላምና ዴሞክራሲ ስም ተከልለው የኖሩበትን ጭንብል አስወልቀህ እርቃናቸውን በማስቀረት ዕውነተኛ ማንነታቸውን ለዓለም ሕዝብ አጋልጥህ አሳይተህባቸዋል:: ይህ ያልጠበቁት አስፈሪ ሽንፈትም እስከአሁን የካዱትን ሰው መሰል አውሬነት ይፋ አድርገው እንዲጠቀሙበት ተገድደዋል:: እንዲህ ያለው አረመኔያዊ ድርጊት መልሶ ያሳፈረው ደግሞ መታፈርን የማያውቁ ማፈሪያዎችን ብቻም ሳይሆን ቀጥረው ያዘመቷቸውንና የሌላቸውን ስምና ክብር እየሰጡ አደላድለው ያሰቀመጧቸውን የቃል ኪዳን ጌቶቻቸውን ጭምር በመሆኑ የተገኘው ድል በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ የመግደል ያክል ነው::



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የኢዴአአህግ እንደተመሠረተ አንድ መልዕክት በኢትዮጵያ ሬጅስተር መጽሔት ማስተላለፌን አስታውሳለሁ፡፡ ይኸውም የችግርህ ሁሉ መፍትሄው መምረርህና ማምረርህ መሆኑን አጠንክሮ የሚያሳስብ ነበር፡፡ እንዳገናዘብኩት በአሁኑ ወቅት በማካሄድ ላይ ያለኸው ትግል ወደዚያ የሚያመራ ይመስለኛል፡፡ የዛሬው መልዕክቴም ያንኑ አባባል ደግሜ ለማሳሰብ ነው፡፡ ምክንያቱም የመደራጃ ስልትና የችግሮችህ ሁሉ መፍቻና የችግር ፈጣሪዎች ሁሉ ማስወገጃ መሣሪያ ነው ብየ ስለማምንበት ነው፡፡

በመሠረቱ ምሬት የብሶት መግለጫና የማምረር የመጀመሪያ ደረጃ ከመሆኑም አልፎ ቆርጠው የሚሄዱበት የትግል ጎራ ሆኖ የሚያስልፍም ነው፡፡ ገበሬው ገብር ባዮችና አሳሪ ፈችዎቹ በዝተው ሲያማርሩት ከሚያሰማቸው እንጉርጉሮዎች ለአብነት ያህል ብጠቅስ፡-

አሞኝ ውሎ አሞኝ ሊያድር ነው ወይ?
አርሶ መብላት እንኳ ጤና ላይሆን ነው ወይ?
ደመና ሲደምን ይወረዛል ገደል፣

ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል፡፡ ማለቱንና አምርሮ መውጣቱን አሳምሮ ያውቅበታል፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ችለህ መቀመጥህና ሰላማዊ ድምፅህን ማሰማትህ እንኳ ለጠላቶችህ ወንጀል መስሎ ከታያቸው ወንጀልህ ሰው ሆነህ እንደሰውነቴ ልኑር ማለትህ እንጅ ሰላማዊ ድምፅህ እንዳለሆነ በትክክል ሊገባህ ይገባል፡፡ እንዲህ ያሉም በመሆናቸው ሰውነትህን (ህልውናህን) ጨርሰው ካላጠፉ በስተቀር ለማያርፉልህ ጠላቶችህ የበለጠ እየመረርክና እያመረርክ እንጅ ሲረግጡህ የማትቆረቁርና የማታንቆራቁር መደላድል፣ ሲቀምሱህ የምትጎመዝዝ እሬት ሳትሆን የምትጣፍጥ ወተትና ማር፣ ሲከፉህ ደግሞ አምቀህ ይዘህ የምታምጥ እንጅ የማታመርና የማትቆርጥ ገር ሆነህ መገኘት የለብህም፡፡ ከእስከአሁኑ በልኑር ባይነት የታገዘ ልልነት ይልቅ በአሁኑ ወቅት በማሳየት ላይ ያለኸው ቆራጥነት ምን ያህል የጠላቶችህን ሠፈር እንዳርበደበደና መሣሪያ አድረገው ሲነግዱ በኖሩበት ሰላምና ዴሞክራሲ ላይ ዘምተው ራሳቸውን እንዳጋልጡ ሊያስተምርህ ይገባል፡፡

እስከአሁን ከአንተ በአንተ ለአንተ ሳይሆኑ ለእርሱ ቆመናል እያሉ ሲያታልሉ የኖሩበትን የዕምነት ደም የለሽ የቆዳ ቀለም ማታለያነት በለየለት የጠላትነት ወንጀላቸው አጋልጠህ ለዓለም የፖለቲካ መድረክ ማሳየትህ ራሱ ብዙ ነገር እንዲያጡ ስላደረጋቸው ድምር ውጤቱ ወደግብህ የሚያቃርብ እርከን መሆኑ ሊያጠራጥርህ አይገባም፡፡

አጥብቄ የምሰጋበት ጉዳይ ቢኖር በራስህ ተጋድሎና በልጆችህ ክቡር መስዋዕትነት ያጋጋልከውን ግለትና ያሳየኸውን ዕድገት አንተው መልሰህ እንዳትገታውና እንዳታበርደው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከሰላማዊ ትግልህ ትምህርት ያገኙት ጠላቶችህ ያን የተቋጠረ ፊትና ወደ ቋያነት ሊለወጥ የተቃረበ የጋመ ግለት ተመልሶ ማየት ስለማይፈልጉ የቀሩህን ጀግኖች በለቀማ አስጨርሰህ የጀግኖች ድህነት ጨርሶ እንዲወረስህ ከማድረግ እንደማይገቱ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ በማድረግ ላይ ያሉትም የህንኑ ነው፡፡

«ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች» ይባላል፡፡ እንደ እኔ ትርጉም ጥልቅ መልዕክት ያለው አባባል ይመስለኛል፡፡ የዱር እንስሳዋ (አራዊቷ) ከአካሏ ተከፍሎ የወጣው ልጇ ተፈጥሯዊ ትሥሥር አስገድዷት ለእርሱ የተወረወረውን ጦር ቀድማ የተቀበለችው እኔ በሕይዎት ቁሜ ልጄ ሲታረድ (በጦር ሲዎጋ) ከማየው ይልቅ ለእርሱ ስል አልፌ ልወጋለትና እርሱ ቀርቶ ሃላፊነቱን ይውሰድ ብላ ወስና መሆኑ ቋንቋው ባያግባባንም የወለደ ስስ አንጀቷ አልችል ብሎ ያስተናገደው መስዋዕትነት አግባቢ ቋንቋ ሆኖ አርአያነቷን ያሳየናል፡፡

አንተ ደግሞ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠርክና የምድር ፍጥረታትን ሁሉ እንድትገዛ ሥልጣን የተሰጠህ ታላቅ ፍጡር በመሆንህ ገኘው ጌታ ራስህን ባለመግዛትህ ከምትገዛት የዱር እንስሳ አንሰህ የአገሪቱ የወደፊት ተስፋ የሆኑትን አበባ ልጆችህን ምህረት ማድረግ ቀርቶ ምህረት የሚያደርግላቸውን እንኳ ለካዱ አረመኔዎች



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

አጋልጠህ በመስጠት እያስቀጠፍክ የእነርሱ ደም ያቀለመውን ጎዳና እየረግጠክና የህን ሁሉ ደም ባፈሰሱት ባለደሞችህ እየተረገጥክ ለመኖር የወለደ አንጀትህ የሚጨክንና የሞራል ግዴታህ የሚፈቅድልህ አይመስለኝም::

ሌላው አብረህ ልታየው የሚገባህ መሠረታዊ ነጥብ ለችግሩ መፈጠርና እየተወሳሰበ መምጣት ብዙ ምክንያቶችና ደርግን ጨምሮ ከሱ የባሱ ግንባር ቀደም ተጠያቂ ወንጀለኞች ቢኖሩበትም ከዚህ ደረጃ ላይ የደረሰው በአንተ የዕድሜ ክልል ማለትም በዚሁ ትውለድ ጊዜ ነው:: ይህም በመሆኑ በዋንኛዎቹ ወንጀለኞች ላይ ላመካኘ ካላልክ በስተቀር አንተም ብትሆን ከድክመቱ ነፃ አይደለህም:: ስለሆነም ምንም ይሁን በማን ይደረግ ቅድሚያ ልትሰጠው የሚገባህ እየተከማቹ የመጣውን የችግር ዕዳ ራስህ ባለዕዳው ከፍለህ ልትጭርስ የሚገባህ መሆኑን ነው:: ከአንተም አልፎ እንደመልካም ቅርስ ለልጆችህ የምታወርሳቸው ከሆነ ግን ሲጨራረሱ እንዲኖሩ ያደረግሃቸው አንተ እንጅ የመጨረስ ኃይልና አቅም ያልነበራቸው ጠላቶችህ አለመሆናቸውን ሰፋ አድርገህ ልታገናዝበው ይገባል::

ጠላቶቻችን የራሳቸው ብቻ የሆነ ዓላማና ግብ አላቸው:: ይኸውም ለማጥፋት አቅደው በዘመቱባቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መቃብር ላይ ታላቋን የትግራይ ሪፐብሊክ መገንባት ነው:: ከዚህ ውጭ የሚታያቸው ራዕይና የሚጥማቸው ማር የለም:: ይህንን ካላደረጉ ደግሞ የፀሐይ ሙቀትም ሆነ ድምቀት ለእነርሱ ብርድና ጨለማ ነው:: ለሰው ልጅ ቀርቶ ለዱር አራዊት እንኳን ጣዕምና ትርጉም ያለው የአካባቢ ሰላማዊ ኑሮ ዶሮ ይመስል ከቤት ታዛ ላለወጡት መንደርተኞች ለመንደራቸው ማደላደያ እስካልሆነ ድረስ እንደ እሬት የሚመራቸውና እንደ አቃቅማ እሾህ የሚወጋቸው ሆኗል::

እነዚህ ሁሉ ለአንተም እንግዳ ነገር አይደሉም:: ይህ መሆኑ በገሃድ እየታወቀ ስለሰላማዊ ትግል ሲነገር የከረመው ነቢዩ ኢሳይያስ «ሰላም ሳይኖር ሰላም ነው ይሉናል::» ያለውን ያዘከረ እንዳልነበር የሰላም ጠላት የሆኑት ጦርነት ፈጣሪዎች የፈፀሙት እልቂትና የፈጠሩት ቀውስ አጋዥ ሆኖ ይቆምልኛል ብዬ አምናለሁ:: ይህን ስል ጦርነት ማካሄድ ነበረብህ ማለቴ አይደለም:: ስለጦርነት ሁለንተናዊ አስከፊነት በወሬ ጠይቄ ሳይሆን በተለያዩ የጦርነት ግንባሮች ተሰልፌ ያዬሁት ስለሆነ እንደዚያ ያለው እልቂት በወገኔ ላይ ደግሞ እንዲደርስ አልፈልግም:: የግል ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ መሣሪያ አድርገው በማሰለፍ እንደ ፋብሪካ ጥሬ ዕቃ በችግር ወላፈን ውስጥ እየቀሰቀሱ ያስጨረሷቸው የአገሪቱ ውድ ልጆች አሁንም ድረስ ያሳዝኑኛል::

ይኸም ሆኖ ለሕዝባዊ ዓላማና ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚከፈል መስዋዕትነት ያድናል እንጅ አያጠፋም:: ይህ ባይሆንማ ኖሮ ጌታችን ምድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ለእኛ መስዋዕት ሆኖ የመስዋዕትነትን አዳኝነት ባላስተማረንም ነበር:: ስለዚህ ያለመስዋዕትነት አገራችንን ማዳንና ነፃነታችንን ማስከበር እንደማንችል ያለማወላወል የምንቀበለው ግዳጅ መሆን አለበት:: መስዋዕትነትን እንድንከፍል የምንገደደው ግን እኛ ፈልገን ሳይሆን ጦርነት ፈጣሪዎች የሚያመልኩት ዕምነት በመሆኑ በእርሱ ተገድዳችሁ ለእርሱ ካልሰገዳችሁ በስተቀር መኖር አትችሉም ስለተባልን ነው:: በእርግጥ መስዋዕትነት ሲባል ለአገር ህልውና የሚከፈል መስዋዕትነትና የግለሰቦችን ፍላጎት ለማሟላት ሲባል አሳልፈው የሚሰጡት ሕይዎት በዓላማውም ሆነ በትርጉሙ ፈፅሞ አይገናኝም:: ምክንያቱም ብዙሓኑን ለማዳን ራስን አሳልፎ የሚሰጡበት ክቡር መስዋዕትነት ሲሆን፣ ራስን አደላድሎ ለማኖር ሲባል ብዙሓኑን እያስቀደሙ የሚያስፈጁበት ደግሞ ራሱን ያላጋለጠ ሥውር የሕዝብ ጠላትነት ከመሆኑም በተጨማሪ መሣሪያ ሆነው ለሚሞቱ ሟቾችም ስምና ትርጉም የለሽ ተራ ሞት በመሆኑ ነው::

ስለዚህ በብርቱ የማሳስበው የተጋፈጥካቸው ችግሮች ሳይበግሩህ የጀመርከውን ትግል ለውጤት በሚያበቃህ የትግል ስልት የበለጠ እያጠናከርክ እንድትቀጥል ነው:: በእርግጥም ይህን ካደረግህ የችግሩን አቀበት ወጥተህ ከተደላደለው ሜዳ መድረስ የምትችልበት ጊዜ እሩቅ እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ:: ይህን ከማድረግህ በተቃራኒ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ትግልህን ካላላሽውና ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ ዳር ቆመህ መመልከትን ከመረጥክ ግን ለጠላቶችህ ሁለንተናዊ ዓላማ መሳካት ራስህን ከፍተኛ በረከት አድርገህ እንዳቀረብክላቸው ሥውር ሊሆንብህ አይገባም።

ቀደም ሲል እንደገለፅኩት የዛሬውን ሕዝባዊ ቁጣህን ከትናንት በፊትና ትናንት አሳይተሃቸው ቢሆን ኖሮ ዛሬ የተፋጠጥካቸው ጠላቶችህና ያጋፋጡህ ችግሮች ሁሉ አይኖሩብህም ነበር። ካለፈ ድክመት ሳይማሩ ቀርቶ ዛሬም ያንኑ አዙሮ መድገመም ግን ከድክመት መማር የሚገባው የሰው ልጅ ራሱን ወደ ድክመት ለውጦታል እንዲባልለት የሚያስገድድ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት አምርረህ የምታዝነው ለተሰውትና አካላቸው ለጎደለው ልጆችህ መሆኑን በእዝነ ኅሊናየ እረዳለሁ። እኔን በበለጠ የሚያሳዝነኝና የሚያሳስበኝ ግን ሁሉንም ልጆችህን ሁሉንም ነገር አሳጥተህ በቁማቸው እንዳትቀብራቸው ነው።

እነሱን የሚተካ መልካም ልጅ አልወጣላቸውም እንጅ ከመልካም ወላጆች የተወለዱት ጀግኖች አባቶቻችን የታሪክ አደራ የሚከብዳቸው፣ እናት አገራቸውን የሚወዱና ለሚያልፍ ችግር ተበግረው የማያልፍ ስማቸውን የማይሠብሩ መልካም ወላጆች ስለነበሩን በዕውነትም እነሱን ከተኩ ወላጆቻቸው የወረሷቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ ለእኛ ተክተናቸዋል ለምንለው ልጆቻቸው አስረክበውን አልፈዋል። አጣያያቂ የሆነው ግን ከእነርሱ ተወልደናል የምንለው እኛ ከሥጋ ቆጠራ ባለፈ በእርግጥም የባህሪ ልጆቻቸውም ሆነን በሁለመናቸው ተክተናቸዋል ወይ? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ነው። አንድም ታሪክ ዋሽቷል አለዚያም ትውልድ ተኮላሽቷል ወደሚያሰኝ ምርምር የተገባውም በዚህ ምክንያት ነው። በብዙ አጋጣሚዎች እንደገለጽኩት ለእነዚያ በሁሉም ነገር ለታደሉት ክቡር ሰዎች የመሠከረ ታሪክ አለመዋሸቱ ባያጠራጥርም የአሁኑ ትውልድ መኮለሸቱ ግን አያጠያይቅም።

አዎ! ተክተናቸዋል ካልን ግን መምሰላችንን ሳይሆን መሆናችንን የሚያረጋግጡ መረጃዎችን ማስቀመጥ የግድ ይሆናል። ከዚህ ጋር አዛምጀ እኛስ እንዳባቶቻችን ለልጆቻችን የምናወርሳቸው ምን ቋሚ ሃብትና ባህል አለን የሚል አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ባነሳ ምክንያተኛው ትውልድ ራሱን የሚከላከልበት መልስ ባያጣም ሀቁ ግን ምንም የሚል ነው። ምክንያቱም እናት አገርን እንዳናወርሣቸው ለዘመናት ሲድሁ የኖሩት ታሪካዊ ጠላቶቻችን እንደአቅዳቸው በጣጥቀው ሊያጠፏት ቀርቶ በእግራቸው እንኳን ሊረግጧት እንዳልቻሉ ሁሉ ዛሬ ግን ከእኛ እጅ ላይ ጥሏት አጋልጠን ስለሰጠናት ይኸውና ቀጥረው ባዘመቱብን ጥቁር ሹምባሾቻቸው አማካኝነት እንደፈለጉ እያብጠለጠሏትና ደብዛዋን ጨርሶ ለማጥፋት እየተጣደፉ ነው። ስለዚህ ታሪካዊ ስሟንና ነባራዊ ቅርጽዋን ካለሆነ በስተቀር በእጃችን የሌለች እናት ሀገር ምኗን ነው የምናወርሠው?

ጀግንነትን እንዳናወርሣቸው ጀግና የሚያሰኘውን ጀግንነት እየሠራን አላስተማርናቸውም። እንዲያውም እንደፈለጉ ሲያምሱንና ሲወርሱን፣ ሲያሥሩንና ሲፈቱን፣ ሲገድሉንና እየነቀሉ ሲያሰድዱን ማየት በዕየለቱ የሚያነቡት መጽሐፍ ስለሆነባቸው በራስ የመተማመን እጦትን እንጅ «**ማን ከማን ያንሳል?**» በሚያሰኝ የሞራል ጥያቄ የታጀበ አይበገሬነትን አይደለም።

የወንድማማችነት ፍቅርን ልማትንና ዕድገትን እንዳታወርሣቸው ደግሞ የራሳቸው ጎን ቀድሞ የሚነግራቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ጓደኞቻቸው ከወላጆቻቸው ያዩት አዝማሚያ ስለሚገባቸው ያው የዎያኔዎች ኢትዮጵያን አለማንና ያው የብሔር - ብሔረሰቦችን ፍቅር መገንባት ካሴት እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሰላም፣ ልማትና ዕድገት የሚባለው ጥቂቶች ብዙሓኑን የሚገድሉበት፣ ብዙሓኑ እየተራበ፣ እየከሳና እየመነመነ ጥቂቶች የሚበለጽጉበት ሥርዓት ማለት ነው። የጣና ሀይቅ፣ የአዋሽ ወንዝና የአድአ ማኛ ማምረቻ ለም መሬት ...ወዘተ. ተፈጥሮ ባደላቸው ጉድብ መሸገው እየተከላከሉ ከመቆየታቸው በስተቀር ሌሎች ሰው ተከል የሆኑ ነገሮች ሁሉ እየተነቀሉ ተግዘዋል። በአሁኑ ወቅት የትግራይን ገዥዎች ያሳስባቸዋል ብዬ የምገምተው ቢኖር እንደአስዋን ግድብ የተጋዘው ንብረት ደለል



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሞልቶ ወደመሃል አገር ተመልሽ ልፍሰስ ቢል በጠላትነት የምናየው ሕዝብ እንዳይጠቀምበት እንዴት አድርገን ገድበን እናስቀረዋለን? የሚለው እንጅ ከኛ ሞልቶ ከፈሰሰስ ቢሄድላቸው ምንም አይደል ብሎ የሚያዝን አንጀትና ይህን ሁሉ አርቆ የሚያስብ ኅሊና አላቸው ብየ አልገምትም:: አቻ የለሽ ክህደታቸውና አረመኔያዊ ድርጊታቸው እንዲህ ያለውን ዕድል እንዲታደሉ ያደርጋቸዋል የሚል ግምት ጨርሶ ባይኖረኝም ባጋጣሚ የትግራይ ድንጋይ ዳቦ ሆኖ ቢገመጥና የደኑ ልማት እንደ ገነት ዛፍ ሁሉን ለመመገብ የሚችል ፍሬ አፍርቶ ቢትረፈረፍ እንኳ ፍርፋሪ የሚያሳጡ በረከተቢሶች እንጅ ፍርፋሪ እናትርፍላቸው የሚሉ ባለማዕዶች እንዳልሆኑ የ15 ዓመት ተመክሮ በቂ ማረጋገጫ ይመስለኛል::

ይህም በመሆኑ ለልጆችህ የምታወርሳቸው ሞልቶ የተትረፈረፈ ሀብት እንደ ፈረስ ጭራ ቁልቁል እየወረደ ሄዶ መሬት በመንካቱ ማለፊያ ያጣ ድህነትን፣ ሀገር አልባነትንና መንደርተኝነትን እንጅ በሔራዊ አመለካከትንና ወንድማማችነትን፣ ልማትንና ዕድገትን አልሆነም:: ስለዚህ ከአሁን በኋላ ማሰብና ማብሰልሰል የሚገባህ በታሪክ ሕያው ሆነው ለሚኖሩት ጀግኖችህ ሳይሆን ሁሉንም አሳጥተህ እርቃናቸውን ልታስቀራቸው ለማይገባህ ልጆችህ መሆን አለበት:: ስለልጅ ካነሳሁ ሌላም የማሳስበው ብርቱ ነጥብ አለኝ:: እነዚያ በሁለመናቸው ያማረባቸውና ሁሉንም በየፈርጁ የሚያውቁበት ብልሆቹ አባቶቻችን የማህበራዊ ኑሮ ክስተቶችን በየመልኩ የሚገልፁበት ሥነ - ውበታዊ አነጋገር ነበራቸው:: በአሁኑ ወቅት እንደ አንድ የራስህ ልጆች በአንተና በወገኖችህ ላይ የሚፈፅሙትን ከሚጠብቁት የማይጠበቅ አሳዛኝ ድርጊት ከዚህ ጋር አዛምጄ ብጠቅስ:-

«***ማሪያም ሞተች አሉን ትሙት ምን እንበላት፣***
***ደም የሚመልሰው ለጇ ከገደላት***» ያሉትን ነው::

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን አጣምረው ለማጥፋት አቅደው ለዘመቱብህ ደመኛ ጠላቶችህ ገዳይ ወታደርና አስገዳይ ካድሬ ሆነው የዘመቱብህ የአንተን ጥቃት መወጣትና ደም መመለስ የሚገባቸው የራስህ ልጆች ናቸው:: ከሚጠበቁት የማይጠበቅ አሳዛኝ ድርጊት ያልኩትም በዚህ ምክንያት ነው::

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ጎሽ ለልጇ ስትል እንደተወጋችው ሁሉ አንተም ለልጆችህ ብለህ ስትወጋ ልጆችህ ግን ዛሬ እያሳደዳችሁ ግደሉ ብለው ከዘመድ አዝማዶቻቸው ጋር ለሚያዳሚቸው የሁላችንም ሁለመና ገዳይ ጠላቶች፣ ነገ ደግሞ እነሱንም እንደሚገድሏቸው እያወቁ መሣሪያ ሆነው የሚገድሉህ ከሆነ በእጅጉ ሊያሳዝንህ እንደሚችል አላጣሁትም:: ይሄም ሆኖ በትንሹ የሚያስበው ትንሹ ልጅህ በትልቁ የሚያስበውን ትልቁን ልጅህን ሲገድለው ማየት የሁለት ወገን ሁለት ጊዜ ሐዘንተኛ እንዳያደርግህ ለገዳዩ ልጅህ አምርረህ ነገረውና አንድ ጊዜ እርምህን አውጣ:: ምክንያቱም የዛሬው ገዳይ ልጅህ ለዘላለማዊ ሟችነቱን ተቀብሎ ራሱን በቁሙ የቀበረው ራሱ ስለሆነ ሁለት ጊዜ ሊያሳዝንህ ስለማይገባ ነው::

በመሠረቱ ችግር በአንድ ወገን ላይ ብቻ ተጭኖ እያደቀቀና አንቆ ይዞ እያንፈራገጠ የሚኖር ቋሚና ዘላለማዊ አይደለም:: የሚመጣበት ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩትም እንደ አመጣጡ አልፎ የሚያሳልፍበት ብዙ መፍትሄዎችም አሉት:: የችግር አስቸጋሪነቱ ግን የማያልፍ ስም ሰብሮና የማይሽር ጠባሳ ጥሎ ማለፉ ነው:: መለስ ዜናዊና አጃቢዎቹም ከዚህ ዓይነቱ ሠባራነትና የታሪክ ዕዳ ቁስል ጠባሳነት ነፃ እንደማይሆኑ እርግጠኛ ነኝ:: እነርሱ ግን ትናንት እንዳልነበሩ ሁሉ ዛሬ ብቻ እንጅ የራሱ ውሳኔ ወሳኝ ሕልውና ያለውን ነገንም ሊኖሩበት እንደማይችሉ የተረዱት አይመስሉም:: ምክንያቱም ያለትናንት ህልውና የሌለውን ዛሬን ብቻ የሚያይ ዳፍንት ዓይነ - ልቦናቸው ነገ የሚሆነውን ሁሉ ሊያሳያቸው ስለማይችል ነው::

ስለዚህ ለጆችህ የሄ ሁሉ አይቀሬ የተፈጥሮ ሕግ አልገባቸው እንደሆነ ግን ሳትሰለች ንገራቸው:: አንተም ብቻ ሳትሆን ወላጆቻቸው ቤተሰቦቻቸውና የቅርብ ጓደኞቻቸው ሁሉ እናት ሀገርን አብሮ ለማጥፋት የዘመቱ ከሃዲዎች፣ ወገናቸውን የፈጁ በደም ዕዳ ተጠያቂዎች፣ የሕዝብን ትግል ለማኮላሸት በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ጦርነት የከፈቱ ሽብር ፈጣሪዎች፣ በአጠቃላይ በብዙ ወንጀል የሚጠየቁ መሆናቸውን አውቀው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

አምርረው እንዲነግሯቸው አድርግ:: ምክንያቱም ነገ የዚህ ሁሉ ዳፋ እነርሱን ጭምር አብሮ እንደሚያዳፋ እነርሱም በበኩላቸው አውቀዉት እንዲቆዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

ለጠላቶቻችን የሚሰጡት የሞያ አገልግሎት ነው:: ያውም ወገናቸውን ብቻም ሳይሆን እነርሱንም ጭምር መልሰው ለሚገድሉ የጋራ ጠላቶች የሚከፈላቸውም ደመወዝ ወገናቸውን እንዲገድሉ የተገዙበት የሕዝብ ገንዘብ ነው:: ወያኔዎች ቢወድቁ ችግር ውስጥ እንደሚወድቁ አድርገው በመንገር ሊያዉሯቸው የሚፈልጉት ራሳቸው ከተጠቀሙባቸው በኋላ የማይፈልጓቸው ጠላቶቻቸው እንጅ ወልዶ ያሳደጋቸው ሕዝብና ሞያቸውን የሚፈልገው አዲሱ ሕዝባዊ መንግሥት አይደለም:: ሌላው ቢቀር ከትግራይ ለትግራይ የተደራጀ ልዩ ኮማንዶ (የግብር ስሙ ጭፍን የተባለለት) በአዲስ አበባና በሌሎችም አካባቢዎች ሰላማዊ ሕዝብ ላይ አዝምተው የፈፀሙት ግፍ የሚያስብና ተገላምጦ ማየት የሚችል ኅሊና ላለው ሰው ትምህርት ሰጭነቱና ጠቋሚ መረጃነቱ ቀላል አይደለም:: *ነገ ደግሞ የነገሮች መልክ ተለውጦ ወደ ታላቋ ትግራይ ሪፐብሊክ ነጎዳው ሲጀምር «እኛንም ይወስዱናል? ወይስ ቀርተን ወደ ማን እንጠጋለን?» የሚለውን ሁሉ እንዲያብሰለስሉት ከማድረግ እንዳትቆጠብ በአጽንዖት ላሳስብህ እወዳለሁ::*

እናት አገራችን ኢትዮጵያ ትናንት በእነዚያ የሰዎች አገር አሰኝተዋት ይኖሩ በነበሩት ታላቆቹ ሰዎች በሁሉም ነገር ታሪክና ስሟ የገነነ ልጆቿም የተወደዱና የተከበሩ ነበሩ:: ዛሬ ግን የሰው እጅ እያየን ከምንኖር ምርኮኞች እጅ ጥሏት የሁሉም ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ችግሮች ሞዴል ሆና እየታየች ነው:: የጦርነት፣ የድርቅ፣ የኤይድስ፣ የጎሳ ፖለቲካ፣ የኋላ ቀርነት፣ የባህሪ ድህነት ... ወዘተ. በአጭሩ በአሁኑ ዘመን እኛ የደኸየነው የሚባልልን በማጣት ነው:: የሚባልብን ግን ሞልቶ ተርፎን እንደኛ ለመሆን የሚፈልጉ በፍፁም የሉም እንጅ ካሉም ለማበደር ወይም በነፃ ለማደል በጣም ሐብታሞች ናቸው የሚባልልን ሆነናል::

በዚህም ምክንያት በሀገራችን የሰውነት ክብርንና ሞትን አርክሶታል:: በየቀኑ እንደቅጠል ከሚረግፈው ወገናችን ውስጥ ሕያው ታሪክ ሠርተው ለዳግማዊ ትንሣኤ ለመብቃት የሚያስችል ክቡር መስዋዕትነት እየከፈሉ ያለፉት ስንቶቹ ናቸው ብለን ብንመራመር የምናገኘው መልስ ጥቂቶች ብቻ ናቸው ከማለት እንደማያልፍ እርግጠኛ ነኝ:: አብዛኛዎቹ የማይቀረውን ሞት እየፈሩ ከሚቀበሉት ይልቅ ደፍረው ቢተናነቁት ኖሮ የሁለት ጊዜ ድል አድራጊ ጀግና ለመሆን በቻሉ ነበር:: የክቡር መስዋዕትነት ድልና ገዳይ ጠላቱን ተናንቆ ይዞ የወደቀ ጀግና ማለት ነው::

እኔ እንደሚገባኝ ሰው መፍራት ያለበት የመዳን ተስፋ ሲኖረው ነው:: አሊያማ ጣምራ ጠላቶቹ ግንባር ፈጥረው እንደማይምሩት ካወቀ ማድረግ የሚገባውን አድርጎ ለማለፍ ራሱን አስቀድሞ ማዘጋጀትና ሳይቀደም ቀድሞ ማለፍ ከንቱ እኖር ባይነት ያላዘናጋው ቆራጥነት ይመስለኛል::

አንድ በዓለም ታሪክ የታወቀ የጦር ጀኔራል ማንነትን በሚፈትን ወቅት የጦሩ አዝማሚያ አላምረው ስላለ «የራስህ ፍርሃት የሚጎዳህን ያህል ጠላትህ አይጎዳህም» ብሎ ወታደሮቹን በማስተማሩ ሊናድ የነበረውን ጦር ሞራል መልሶ ለመገንባት እንደቻለ ከአንድ መጽሔት ማንበቤን አስታውሳለሁ:: በቅዱስ ወንጌልም *«ሕይወቱን የወደደ ያጣታል፣ ሕይወቱን የጠላ ግን ያድናታል»* እያለ ያስተምራል:: ስለሆነም በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊ ትርጉም መዳን የሚቻለው እራስን ማቸነፍና መግዛት ሲቻል መሆኑን እንረዳለን:: ከዚህ ውጭ አንድ ሰው የሰውነት ሥነ - ተፈጥሮውን ዘንግቶ በእኖር ባይ ተስፈኝነት በሽታ ከተለከፈ ቅድሚያና ትኩረት የሚሰጠው ሕይወቱን ለሚታደግለት ፍቱን መድሃኒት ሳይሆን በሽታውን ለሚያባብስ ፍርሃት ይሆናል ማለት ነው::

አንድ የነፃ ትግል ታጋይ አስቀድሞ እወድቃለሁ ብሎ ከአሰበና የሚወድቅበትን ቦታ መቃኘት ከጀመረ ይወድቃል እንጅ አይጥልም:: ምክንያቱም ለሞራል ጉልበቱ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የመገበውና ለሚማትር ዓይኑ ያሳዬው መውደቅንና የሚወድቅበትን ቦታ እንጅ መጣልንና የሚጥለውን ተፋላሚ ደካማ ጎን አይደለምና ነው፡፡

ከሕይዎቴ ገጠመኝ ልምድ አኳያ ለሞራል የምሰጠው ትርጉም የአሰቡትን ማድረግ የሚያስችል የማያለቅ የመንፈስ ምግብ ነው፡፡ በጉልበትነቱ ረግጦ ለሚቆምና ለይቶ ለመምታት የሚያስችል ፋና ወጊም ነው፣ ራሰን መግዛት የሚያስችል ልቦና ሰጥቶ የአሰቡትን እንዳሰቡት ለማድረግ የሚያሰችል ኃይል ሰጭም ነው፣ የአኩሪ ታሪክ ስም አዉጭ፣ ሕይዎት ሰጭና ውበት አልባሽም ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ማድረግ የሚያሰችል ሁሉም ነው ብሎ መደምደም ይችላል እላለሁ፡፡

እኔ እንደሚገባኝ መቸነፍ በአብዛኛው የሚመጣው ከሞራል ድህነት ነው፡፡ ለመቸነፍ የምሰጠው ትርጉም ግን ሰው በእምነቱ ሲላላ፣ ዓላማውን ሲስት፣ በሞራሉ ሲደኸይና እራስን ማቸነፍ አቅቶት እራሱን ያህል ለማይሆን ጠላቱ ምርኮኛ ሆኖ እጅን ሲሰጥ ነው፡፡ ከእነዚህ ነፃ የሆነ ጊዜያዊ የኃይል አሰላለፍ ሚዛን ማጋደል ግን መቸነፍ ሳይሆን አቸነፍኩ ብሎ የሚመካውን ጠላት ሰርጅቶ ለመጣል የሚያስችል አጋጣሚ መጠበቅ ነው፡፡ የግንቦቱን ሕዝባዊ ምርጫ በዋቢነት ብጠቅስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተቸናፊነት እጁን ሳይሰጥ በኅሊናው ሸፍቶ ኖሮ አጋጣሚው ሲገጣጠምለት የተጠቀመበት እርምጃ ማረጋገጫ ይሆንልኛል በየ አምናለሁ፡፡

በአጠቃላይ ለጉዳት አጋልጦ ሰጥቶ እንድትጎዳ የሚያደርግህ የራስህ ፍራቻና ጥርጣሬ ሲሆን ነፃነትህን የሚያስመልስልህና ክብርህን የሚያቀዳጅህ ደግሞ በራስህ ጥንካሬ የሚመራ ትንቅንቅ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ አሁንም በድጋሜ አጥብቄ የማሳሳበው ወደድል እርከን ያራመደህ የመጀመሪያው እርምጃህ ሳይሸረሸርና ሳይረግብ የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ነው፡፡

መስዋዕትነት አዳኝ እንጅ ገዳይ አለመሆኑን ቀደም ሲል አመልክቻለሁ፡፡ በመሠረቱም ሞት የሚፈራው አሳፋሪ ሲሆንና ሁልጊዜም ብቸኛ ሟች ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡ እንደ ወደቁ ላለመቅረት የሚደረገው ትንቅንቅ ግን ቢቻል ከአለሙት ግብ ላይ የሚያደርስ፣ አለያም ተያይዞ ከመውደቅ ላይ የሚያደርስ ከሆነ ለጠላቶቻችን ትምሕርት የሚሰጥ ከመሆኑ በተጨማሪ ትርፍና ኪሣራው የማን ሊሆን እንደሚችል ሊገባህ ይገባል፡፡

ከዚህ ሁለገብ መልዕክት አኳያ የራሴንም የሕይዎት ገጠመኝ ትምሕርት ሊሰጥ ይችላል በሚል ቅን ኅሊና በመጠኑ መጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ የ69ነኛ ሚሊሺያ ብርጌድ አዛዥ ሆኘ በምሥራቅ ጦር ግንባር ተሰልፌ በነበረበት ወቅት እግረኛ ከእግረኛ ጋር ብቻም ሳይሆን ታንክ ከታንክ ጋር ተላትሞ እስከሚፋለጥ ድረስ ተዋግቼና አዋግቸ አልሞትኩም፡፡ በወቅቱ ፊት ለፊት ተናንቆ የሚወድቁበት እንጅ ግንባር አጥፎ የሚናዱበት የተስቦ በሽታ ስላልነበር ይዤው ከተሰለፍኩት 2345 የብርጌዱ አባሎች ውስጥ 580 ሲቀሩኝ ነው ጅጅጋ የተባለውን ታዋቂ ወታደራዊ መሬት በጠላት ጀርባ ገብተን ብትንትኑ እንዲወጣ በማድረግ ለማስለቀቅ የቻልነው፡፡ መረጃውን ከቁጥር አንፃር መግለፄ ግድፈት መሆኑ ቢገባኝም ለዚያ እንደነፃ የትምሕርት ወረዳ እንጅ እንደመተላለቂያ የጦርነት ጎራ ሳንቆጥር ያካሄደነውን ትንቅንቅ ለመግለጽ ስል በመሆኑ በጠየመ መልኩ እንደማይታይብኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ስለዕውነትነቱ ዋቢ መረጃዎችን መጥቀስ ቢያስፈልግ ጀኔራል ታዬ ጥላሁን ሀገር መከላከያ ሚኒስትር የነበሩ፣ ጀኔራል መስፍን ገበረ ቃል የምሥራቅ ጦር ግንባር የዘመቻ መኮንን የነበሩትን ብቻም ሳይሆን በሽሬ ግንባር ተሰልፎ ክቡር መስዋዕትነት ከፍሎ ያለፈውን የጀኔራል ኃይሉ ከበደን ክቡር አጽም ሕይዎት ዘርተህ መሥክር ብሎ መጥራት ይቻላል ብየ አምናለሁ፡፡ በእርግጥ ከኋላ መጥተው ባንዲራ ሲሰቅሉና ሜዳሊያ እንደራሽን ሲታደል ግን አላሰለፉኝም፡፡

የደቡብ ጎንደር ኢሠፓ ኮሚቴ አንደኛ ጸሐፊ ሆኘ በምሠራበት ወቅት እንደ ሲቪል ሠራተኛነቴ ቢሮ ሆኘ አመራር የምሰጥ ብቻም ሳልሆን ከሚዋጋው ሠራዊት መካከል እየተገኘሁ ችግሩን እጋራ ስለነበር በሁለት ቀን ልዩነት ሰባት ቦታ ላይ ቆስያለሁ፣ ግን አልሞትኩም፣ ቁስሌንም ምክንያት አድርጌ ከችግሩ አፎት አልዞርኩም፣ ፊቴን አዙሬም አልሸመጠጥኩም፡፡ ይልቁንም ባልተጠበቀ ሁኔታ የተናደውን ኃይል እንደገና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

መልሽ ለማቋቋምና የሺምቅ ውጊያ ለመቀጠል ሄጀ የተማገድኩት ወደችግሩ ቋያ ነው:: ያቀድኩትን ለማካሄድም ብዙ እልህ አስጨራሽ ችግሮች ተፈታትነውኛል:: የህም ሆኖ ሌት ተቀን ሲያድኑኝ የነበሩት ጠላቶቸ ማርከው ሊበቀሉኝ አልቻሉም::

የኢትዮጵያ መልካምድራዊ አቀማመጥና የተፈጥሮ ሀብት ከገዛብን ግንባር ቀደም ጠላቶቻችን አንዷ በሆነችው ሱዳንም ያጋጠመኝ ፈተና እስካሁን ከገለጽኳቸው ችግሮች ሁሉ የባሰ እንጅ የቀለለ አልነበረም:: ለምን ወደዚያች አገር ለመሄድ እንደተገደድኩ ቀደም ሲል በዝርዝር ገልጫለሁ:: ከሄድኩ በኋላ የተጋፈጥኳቸው ችግሮች ግን ያጋጥሙኛል ብየ ካሰብኳቸው ጠላቶቻችን ጋር የተገናኙም ብቻም ሳይሆኑ በማንኛውም መልኩ ራሳቸውን ክደው የሰው አገር ሰው ከሆኑ ወገን መሰል ጠላቶችም ጋር ነበር::

እንደሚታወቀው የሱዳን አገር ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት መከበር እታገላለሁ የሚል የፖለቲካ ሰው ቀርቶ በቤት ሠራተኛነት ተቀጥሮ ለመኖር እንኳ የምድር ፍዳ የሚከፈልባት ሀገር ስትሆን፣ ለሱዳኖች ታማኝ ሰውና ጽኑ ወዳጅ ሆነው ራሳቸውን ወደሱዳንነት ለለወጡት ስመ ገናን የስም ታጋዮች ግን አደላድሎ የሚያኖር እንጅ እንደ እኔ ለአጭር ጊዜ እንኳ የመቆየት ዕድል አሳጥቶ ለእሥር የሚዳርግ አልነበረም:: ምክንያቱም የኢትዮጵያዊ ሱዳኖች የፖለቲካ ሥራ አዳዲስ ድርጅቶች ተቋቁሙ በተባሉ ቁጥር እንደወተተት ዝንብ ዘልለው እየተዘፈቁ አለን እያሉ ለመኖርና ጣምራ ንግድ እያካሄዱ ገቢያቸውን ከማጠናከር ባለፈ ዕውን ለሀገር የሚበጅ ቁም ነገር ሠርተው ወደአገራቸው ለመግባት አልነበረም:: እንደዚያማ ቢያደርጉ ኖሮ ከወያኔዎችም ሆነ ከሱዳን መንግሥት ስትራቴጂካዊ ግብ ጋር ሰለሚቃረን አንድም እንደ እኔ ተይዘው እንዲሰጧቸው ጥያቄ ይቀርብባቸው ነበር፣ ወይም በእሥር ቤት ታጉረው ይሰቃዩና ተነቅለው እንዲሰደዱ ይገደዱ ነበር:: ስለዚህ ሱዳን ሀገር ለመኖር ከተፈለገ አንድም እንደ ኢትዮጵያዊ ሱዳኖች የእነርሱን ግብር ወርሶ እንደ እነርሱ ወደ ሱዳንነት መለወጥ፣ አሊያም የሚመጣውን ችግር ሁሉ መጋፈጥ የግድ ይሆናል:: በእኔ ላይ የተፈፀመው ይኸው ነው::

ስለሆነም እነዚህን ሁሉ በቆራጥነት ቁሜ እያስተናገድኩ ይኸውና እስካሁን በሕይወት አለሁ:: ከእነዚህ ሁሉ ፈተናዎች ያወጣኝ አምላክ የተመሰገነ ይሁንና በየሄድኩበት የሚታደገኝ የጀመርኳቸውን አገርንና ሕዝብን ለመታደግ አስተዋፅዖ ያላቸው ሥራዎች እንዲሳኩ የምጥርና ስም ያለው ሞት እንድሞት የምመርጥ እንጅ ተሸሽጌ ሕይዎቴን ለማዳን የማምጥ ወይም ፊቴን አዙሬ የምፈረጥጥ አለመሆኔን ስላወቀልኝ ይመስለኛል::

ትውልድን ማጫራስ ዓላማቸው አድርገው የተነሱ አገር አጥፊዎች የፖለቲካ ተፎካካሪዎቻቸውን ብቻም ሳይሆን ቀበሌ ጽ/ቤት በራፍ ላይ ቆመው የሚጠብቁትን ምስኪን ዘበኞች ሁሉ መጨረስ አለብን ብለው በዘመቱበት ወቅት እውነተኛው ምሑርና ውድ የኢትዮጵያ ልጅ የነበሩት ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን የተናገሩትን አቢይ መልዕክት ከእኔ የሕይዎት ገጠመኝ ጋር አዛምጄ ብጠቅስ:- «ታጋይ ሞቱን በፀጋ የተቀበለው ሕየዎቱን ለትግል አሳልፎ የሰጠ ጊዜ ነው::» ያሉትን አስታውሳለሁ::

ስለዚህ እኔም አንድ ቀን እንደምሞት ያወቅሁት ሰው ሆኘ መፈጠሬን ካወቅሁበትና መሞት የማይገባውን ሕዝብና መጥፋት የማይገባትን እናት ሀገር ማዳን አለብኝ ብየ ቃል ኪዳን ከገባሁበት ቀን ጀምሮ ነው:: ይሄም በመሆኑ ቀደም ሲል በጠቀስኳቸው ተፈታታኝ የችግር መስኮች ከጎሊናዬ ጋር ስሟገት የነበረው ስሜን የሚያውልልኝ የሞት ዓይነት ለመምረጥ እንጅ የማይቀረውን የተፈጥሮ ሀብት አስቀራለሁ ብየ አልነበረም:: ወድጀም ሳይሆን ከወላጆቸ ቤትና ከአካባቢው እየተማርኩ ያደግሁት ይህንኑ በመሆኑ ነው::

ይህንን ስል መኖሬን ጠልቸው አልነበረም:: እንድጠላው የሚያደርግ ችግርም አልነበረብኝም:: እንዲያውም በብዙ ምክንያቶች መኖሬን በጣም እፈልገዋለሁ:: ሌላው ቢቀር ወንድሞቻቸውን በመግደል የታወቁት የቃኤል ግብር ወራሾች በአስተዛዛቢው ወቅት የሚፈጽሙትን አስተዛዛቢ ድርጊት ሁሉ ከማየት ጀምሮ እኔንም በእጅ አዙር



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

አስገድለው በድብቅ ለመቅበር ያቀዱት ሤራ ሁሉ መክኖ ቀርቶ ገዳይ ጠላቶቻችንን ቆሜ ማየቴና አፈራራጅ ጊዜ መጠበቄ እራሱ መኖር ያስገኘው ውጤት በመሆኑ ነው። «*ሲሆን በእኛ ጊዜ በቀር በልጃችን፣*
*ይዘገያል እንጅ አይቀርም ደማችን።*»
የሚባለውም እንደዚህ ያለው ትውልድ የማይረሳውና የማይደርቅ የደም እዳነቱ ጊዜን የሚጠብቅ አፈራራጅ ግፍና በደል ሲፈፀም ነው።

በአጠቃላይ መኖር ሲባል ግን የሚደረግበትን ሁሉ አሜን ብሎ እየተቀበሉና የሚደረገውን ሁሉ እንዳላዩ እያዩ እነዚህን ሁሉ በሚያደርጉ ጠላቶች ጫማ ሥር ወድቆ እየደቀቁ መኖር ማለት አይደለም። መኖር ከተባለ የተሟላ ክብርና ሰብዕናውን የተላበሰ መሆን አለበት። በማንኛውም መልኩ ሲገመገም እንዲህ ያለ ሀገራዊ ሀላፊነት፣ ሕዝባዊ ወገናዊነትና ጠቃሚ ጎን አላቸው የማይባልላቸው ደመኛ ጠላቶች በላዩ ላይ ተፈናጥጠውበት እንደፈለጉ የሚያብጠለጥሉት ኑሮና ያለውሳኔ የሚወሱኑበት ሕይዎት ግን ሰው ሠራሽ ሰውነት (በዘመኑ የቴክኒዮሎጅ አጠራር ሮቦት) እንጅ በተፈጥሮው ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ክብር ያለው ነው ማለት ፈጽሞ አይቻልም።

ስለሆነም የትግሉ ዓላማ በሁለመናው ተራቁቶ በመድቀቅና ተጥሎ በመረገጥ ላይ ያለውን ሰው የነበረ ሰውነት መልሶ ሰው ለማድረግ ከሆነ የሚጠይቀው መስዋዕትነት ሁሉ እየተከፈለበት ሕዝባዊ ትግሉ መቀጠል አለበት። ምክንያቱም እራስን ከጣሉና እንደወደቁ ከቀሩ ከላይ ከላዩ እየረገጡ ጨርሰዉ የሚያደቁና አደላድለው የሚቀብሩ አይምሬ ጠላቶች የበዙበት እንጅ ቆፍረው የሚያወጡና አቃንተው የሚያቆሙ ጽኑዕ ወዳጆች ያየሉበት ጊዜ አለመሆኑ በአንክሮ ሊዘከር ይገባል።

እነዚህን ሁሉ የጠቃቀስኩት በዚህ አጋጣሚ ታሪኬ እንዲታወቅልኝ ፈልጌ ሳይሆን ስለተፈራ የማይዳን፣ ስለተደፈረም የማይሞት መሆኑን በማስረጃ አስደግፌ ለመግለፅ ስል ነው። መቸም ቢሆን ከደመኛ ጠላት ሥውር መርዝና በይፋ መግደያ ጥይት እንጅ ለሚያሰቃይህ ህመም ፍቱን መድሃኒት፣ በችግር ውጋት ለተዳከመው ጎንህ ማገገሚያ የሚሆን ኬክና ብስኩት እንደማይታደልህ ጠንቅቀህ የምታውቅ ይመስለኛ ል። ፊት ለፊት የሚጋፈጣቸውን ቀርቶ በጎዳና ላይ ሲያልፍ ፊቱን አጠቆረብን የሚሉትን፣ ቤተክርስቲያንና መስጊድ ገብተው ቃለ - እግዚአብሔር የሚያሰሙትንና በትምህርት ገበታቸው ላይ የነበሩትን ህፃናት ያልማሩ አይማረኝ የሚባልላቸው አረመኔዎች በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ሰላማዊ ሕዝብ ላይ ታንከኛ ጦር ያዘመቱበት፣ እግረኛ ወታደሮቻቸው የታጠቁት መሣሪያ የማይበቃ ሆኖ ሳይሆን በታንኩ ሰንሰለት ጭምር እየደፈጠጡ ከመጣል እንደማይመለሱ የለየለት ጠላትነታቸውን ለማሳወቅ ሲሉ ያደረጉት መሆኑ ሊያጠራጥረን አይገባም።

ሰላማዊ ትግሉ የተጀመረው እነዚህን ሁሉ ሲያደርጉ እንደኖሩ ሁሉ ወደፊትም ከማድረግ እንደማይመለሱ እየታወቀ ከሆነ በአሁኑም ወቅት በማድረግ ላይ ያሉት አዲስ ሊሆንብን አይገባም። ስለዚህ አብሮ የቆየና የተለመደ ጠላትን ደካማ ጎኑን እየፈለጉ በመሸንቆር አብሮ እንዲቆስል ማድረግ እንጅ በአፍጢሙ ሊደፉ ከተቃረበ ውድቀቱ ተመልሶ ተቃንቶ በሁለት እግሩ እንዲቆም ለማድረግ የሚችልበት ዕድልም ሆነ እድሜ መስጠት ለእርሱ መጥፊያ ጦስ ቤዛ ሆኖ እንደማለፍ የሚቆጠር ነው።

*ነፃነት ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!* ጽሑፌን የማጠቃልለው በሁሉም ችግሮችና ችግር ፈጣሪዎች የተቸገርከው አንተ ብቻ የመሆንክን ያህል፣ የሁሉም ችግሮችህ መፍትሄ ሰጭ ሊቅ፣ የሁሉም በሺታዎችህ አዳኝ ፍቱን መድሃኒት፣ ሁሉንም ጠላቶችህን እንዳሰላለፋቸው መክተህ በድል አድራጊነት የመውጣት ኃይልና ችሎታ ያለህ አይበገሬ ሠራዊት መሆንክን ሊያሳይ በሚችል ቃል ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ በማንም ይሁን መቼ ችግሮችህ በዓይነትም ሆነ በመጠን እየተደጋገፉ መጥተው ከዚህ ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው። ከአንድ ቦታ ላይ ተቀጭተው ካልወደቁና ተነቅለው ካልደረቁ በስተቀር እስከአሁን ያደረጉትን ሁሉ እያደረጉ መቀጠላቸው አይቀሬ ነው። ይህን የማድረግ ግንባር ቀደም ሃላፊነትና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ግዴታ ያለብህ ግን አንተ ነህ:: በንፁህ አዝመራው ማህል የበቀለን እሾህና አሜኬላ ማዶ ያለ ሰው መጥቶ እንዲያርምለት የሚጣራ ገበሬ የለምና:: ስለዚህ ችግሮችህን ሁሉ ከሥራቸው መንግሎ ጥሎ የተደላደለ ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር የሚቻለው በአንተ ሁለንተናዊ ጥረትና ትግል ነው:: ሌላው ቁርጠኛ ሆኖ ከጎንህ የተሰለፈው ኃይል ድጋፍ ሰጭህ እንጅ የአንተን ሃላፊነት ወስዶ የሚወጣና ሚናህን የሚጫዎት አይደለም::

በዙሪያ - ገባህ ያደሩብህን የተወሳሰቡ ችግሮች በአጭሩ ለማመልከት ያህል ደሞ ባቃባ የጎሣ ፖለቲካ ተዘፍቀሃል፣ በእርግጥ የተቃባህ ሌሎች ያፈሰሱት ደም ተፈናጥቆ እንጅ የአንተ ደም ከመፍሰስ አልፎ ሌሎችን አድምተህ እንዳልተቃባህ የአደባባይ ሚስጥር ነው:: መንደርተኞቹ ጠባቦች ከሰፊው ሕዝብ ጋር በሰፊው የሕዝብ አዳራሽ አብረው መኖርን ስላላወቁበት ወደተፈጠሩበት ደደቢት ማዝገማቸው አይቀሬ ግዴታ ነው:: ይሄም ሆኖ የበተኑትን የጎሣ እንክርዳድ ከሥሩ ለመንቀልና ንጹህ አዝመራ አምርቶ ጤናማ ሕይዎት ለማምራት በሰፊ ትዕግሥት የታጀበ ከፍተኛ ጥረትን ይጠይቃል:: በእርግጥ የጎሣ ፖለቲካ ቀርቶ የአሮጌ ቤት ፍራሽ ጋሬጣ የደደቀው የእግር ቁስል እንኳ እያመረቀዘ ለብዙ ቀናት እንደሚያስነክስ ግልጽ ነው:: ይሁን እንጅ ትዕግሥቱም ሆነ ጥረቱ ቁስሉን ለማዳን እንጅ ሲቋስሉ ለመኖር መሆን የለበትም::

በብዙ ችግር የተዳከመው ጎንህ የሚያስተናግዳቸውና ሰላም አጥቶ የታወከው ህሊናህ የሚያብሰለስላቸው ሌሎችም በርካታ ችግሮች አሉብህ:: በኤድስ በሺታ የሚረግፉት ልጆችህ ሐዘን ከአንጀትህ አልወጣም:: ዛሬም ሐዘንተኛ ነህ:: በእጅጉ የሚያሳዝነው የሚያላቀሱህ ቀርቶ የሚደርሱህ እንኳ አለማግኘትህ ነው:: የሚያስለቅሱህ ግን በገፍ ናቸው:: የደቀቀው ማኅበራዊ ኑሮህ ራሱ ሚዛንህን ስለአዛባው አሰታውለህ ለማየትም ሆነ እየመረመርክ ለመራመድ የማያስችል ብዥታ ፈጥረውብሃል:: ሌላው የመግደያ ስልት የግብር ጫና፣ የሥራ አጥ ልጆችህ የሞራል ድቀት፣ የሠራተኛው የሥራ ዋስትና እጦት፣ የህፃን ልጆችህ ት/ቤቶች የወታደር ጦር ሠፈር መሆን ... ወዘተ. እነዚህ ሁሉ ተጠቃለው ሲታዩ አንተን እንደወር ግቡ ነፍሰ ጡር ሴት ተቀን የሚያስጨንቁ እንደሆኑብህ ደህና አድርጌ እረዳለሁ:: የማቀርብልህ የመፍትሄ ሃሳብ ግን ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች ብልሃት ፈጣሪ ሆነህ የምትገላገላቸው፣ ዶክተር ሆነህም የምታገላግለው አንተው አንተን ነው::

ከዚህ ጋር አዛምጀ ወር ግቡዋ ሴት ከዘጠኝ ወር ሸክሟ ይልቅ በእነዚህ ቀናት እጅግ በጣም ተጨንቃ የምታምጠው ወልዳ ለመገላገል ነው? ወይስ ተሸክማ ስትማቅቅ ለመኖር? የሚል ጥያቄ ባቀርብልህ መልስህ ለመገላገል ነው እንደሚል አያጠራጥረኝም:: ስለዚህ እኔም የምለው ይኸንኑ ነው::

ጠላቶችህ 15 ዓመት ሙሉ በብዙ ችግር ሲያስጨንቁህ ኑረዋል:: ያስረገዙህ ችግር በዓይነትም ሆነ በመጠን እየጨመረና እየተወሳሰበ መጥቶ ዕድገቱን ስላሟላ በምትገላገልበት ወቅት ላይ ደርሰሃል:: ከዚህ በኋላ ምርጫው የአንተ ነው:: አንድም ያስጨነቀህን ያህል ተጨንቀህ አውርደህ መገልገል፣ አለበለዚያም ጊዜያዊ ጭንቀቱን በመፍራት ውጪ አስቀራለሁ ብለህ የምታደርገው ከዕድገት ህግ ጋር የሚቃረን አጉል መግተርተር ዕድገቱን ጭርሶ ከዚህ በኋላ የሚቆይበት ዕድሜ የሌለው ችግርህ በሆድህ ውስጥ እንዳለ ሞቶ አንተንም ጭምር ይዞ እንዳይሞትና የባሰ ችግር ላይ እንዳይጥልህ በብርቱ አስብበት::

ወንድማቸው አብርሃም ያየህ በአንድ ወቅት የደርግ ፖለቲካ ለወያኔ ሲሳይ ነው ያለውን አስታውሳለሁ:: የአንተ በየዕለቱ ሐዘን መቀመጥ፣ ጨኸት ስቃይና ጭንቀት የጠላቶችህን ፍላጎት የሚመግብና ሕይዎት የሚያለመልም ወይንና ፍትፍት እንጅ «እረ መሯቸዋልና እናስብበት» የሚያሰኛቸው አልሆነም:: ይህን የሚያሳይና ስለዚህ የሚያስብ ኅሊናም የላቸውም:: እንግዲያውማ እርቀ - ሰላም እንዲወርድና ወደነበርንበት የወንድማማች ፍቅር እንዲመለሱ 15 ዓመት ሙሉ ተለምነው ነበር:: ጠላትነትህን እንጅ ወንድማዊ ፍቅርህን ያልፈለጉት ጠላቶችህ ግን ዓላማ አድርገው ያነጣጠሩበትና ገድለው ለመቅበር የሚረባረቡት በሰላም፣ በዴሞክራሲና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በወንድማማችነት ፍቅር ላይ ነው:: ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ስንል እንዚህን ሁሉ አካትቶ የያዘ ነው ማለታችን ነበር:: ለእነሱ ግን ትርጉም የለሽ ነው::

ታዲያ ለእነዚህ ቆርጠህ ካልተጋደልክ ምኑን ኖርከው? ከእነዚህ ውጭ በነፃነት ቀርቶ እንዲያው ለመኖር ያህል ልኑር ብትል እንኳ አትችልም:: ምክንያቱም ጠላቱ ከወደቀበት ተነስቶ ነፍስ እስኪዘራ ድረስ ዕድሜና ፋታ የሚሰጥ ሞኝ ጠላት የለምና ነው::

ስለዚህ የችግርህን ምጥ ከነስንጉ አውጥተህ ጥለህ ተገላገልና ጤናማ ሕይዎት ዝራ:: እኔ የማምነው በመሠረታዊ ለውጥ ነው:: ዝናብ እንደመታው ጎታ (ድብኝት) እየቆየ የሚፍረከረክ ጥገናና ለጠላቶቻችን ጊዜ መግዣ የሚሆን ሰላማዊ ድርድር መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ያመጣል ብየ አላምንም:: በመሠረቱም በማናቸውም ነገር ከማይታመኑት ዕመነተቢሶች ጋር ተደራድሮ በምን ሊያስተማምን በሚችል መቋጫ ውል ላይ ሊደረስ እንደሚቻል እራሱ አጠያያቂ ነው:: መጀመሪያውኑ ለመወያየት እንኳ በትርጉም ባያግባባም አንድ ዓይነት የዓላማ ቋንቋ መናገርን ይጠይቃል:: ***ስለሰላማዊ ትግልም ሆነ ድርድር በተወሳ ቁጥር በኀሊናየ የሚጉላላው መሠረታዊ ጥያቄ በኢትዮጵያን ማጥፋትና በኢትዮጲያን ማዳን መካከል ያለውን ምሥራቅና ምዕራብ ማገናኘት ቀርቶ ማቀራረብ የሚቻለው እንዴት ብሎ ነው?*** የሚያሰኘ ጥያቄ በውስጡ ስላለበት ነው::

ይህን ስል ችግሮች በውይይት አይፈቱም የሚል ግትር አቋም ኖሮኝ አይደለም:: በልጠው የማይበልጡበትን መጀመር ግን በጠላት ተበልጦ መሞኘትን እንጅ ከጠላት በልጦ መብለጥን የማያስገኝ በመሆኑ ነው::

በመጨረሻም እንዳለፉት ዓመታት ድምፄ ጠፍቶና ኮቴየ ርቆ እንደማይቀጥል ተሰፋ አደርጋለሁ::

በጀግኖች ልጆቿ ክቡር መስዋዕትነት የእናት አገር ኢትዮጵያ ታሪካዊ አንድነት ለዘላለም ተከብሮ ይኖራል!!

የሰው ዘር ዳኛ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ፍርድ አያሳጣን፣ አሜን!



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com